ኢፕድ
# አዲስ ዘመን
ረቡዕ 81ኛ ዓመት ቁጥር 250 ግንቦት 10 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# የውጭ ተጽዕኖዎች የለዘቡ ቢመስልም በተለያየ መልኩ መቀጠላቸውን መንግሥት አመለከተ


ፎቶ፡ሐዱሽ አብርሃ

የውጭጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ላይ የሚሰነዘረው የውጭ ተጽዕኖ የለዘበ ቢመስልም አሁንም ጫናው ባለመቆሙ ሀገሪቱ የተጠናከረ የዲፕሎማሲ ሥራ እንደሚጠብቃት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አመለከተ። ግንኙነቱን ወደ ጠንካራ የኢኮኖሚ ትብብር ለማሸጋገር የተለያዩ ተግባራት እየተከናወኑ መሆኑን ጠቁሟል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርን የዘጠኝ ወራት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ትናንትና ያቀረቡት ም/ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጪጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን እንደገለጹት፤ ከበርካታ ርብርብ በኋላ ጫናዎቹ በተወሰነ ደረጃ የመለዘብ ምልክት ቢያሳዩም ተጽዕኖዎቹ አሁንም በተለያየ መልክ ቀጥለዋል።

እነዚህን የውጭ ጫናዎች ለመቀልበስ አስፈላጊውን የዲፕሎማሲ ሥራ በተጠናከረ መንገድ ማከናወን ከሁሉም ይጠበቃል ሲሉ ተናግረዋል።

በሰሜኑ ኢትዮጵያ የተከሰተውን ግጭት ተከትሎ አንዳንድ የምዕራቡ ዓለም አገራት፣ የሰብዓዊ መብት ድርጅቶችና ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃን መንግሥት ሰብዓዊ መብቶችን እየጣሰ መሆኑንና ዕርዳታ ለዜጎች እንዳይደርስ እንቅፋት እየሆነ ነው የሚል ክስ እንደሚያቀርቡ አቶ ደመቀ ጠቁመዋል።

የተቀናጀ የክስ ዘመቻ በማካሄድ የሰብዓዊ መብት ጉዳይን እንደፖለቲካ መሳሪያ በመጠቀም ጫና ሲያሳድሩ መቆየታቸውን ተናግረዋል።

አሁን ላይ ግን አገራቱ ኢትዮጵያ ላይ የሚያደርሱትን ጫና ለመቀነስና ግንኙነታቸውን መልሶ የማሻሻል አዎንታዊ ለውጦችን ማሳየት ጀምረዋል ያሉት አቶ ደመቀ፤ ሆኖም አሁንም በጀርባ የተለያዩ ተጽዕኖዎችን ለመፍጠር እየተንቀሳቀሱ መሆኑን ገልጸዋል።

ይህንን ጫና ለመመከት ለአሜሪካ ሴኔትና ተወካዮች ምክር ቤት እንዲሁም የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ኃላፊዎችን ጭምር የማነጋገር ሥራ ተሰርቷል። ይህ አይነት ጥረቶች ዳያስፖራውን ባሳተፈ መልኩ በተለያዩ አገራት ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታውቀዋል።

በተለያዩ ፍላጎቶችና የፖለቲካ አሰላለፍ ለውጦች ምክንያት እንዲሁም የዓለም ስርዓት ተገማች ባለመሆኑ የዲፕሎማሲ ሥራችን በዕጅጉ ፈታኝ ሆኖ መቀጠሉ አይቀሬ ነው ያሉት አቶ ደመቀ፤ ውስጣዊ አንድነታችንን የማስጥበቅ እንዲሁም ሰላምን ከማረጋገጥ ጎን ጫና ፈጣሪዎቹን በማስገንዘብና በማለዘብ ላይ የተመሰረተ የውጭ ግንኙነታችንን አጠናክሮ መቀጠል ይገባል ብለዋል።

የዲፕሎማሲያዊ ጫናዎችን በመከላከል ረገድ የዳያስፖራው ሚና ከፍተኛ ነበር ያሉት አቶ ደመቀ፤ ዳያስፖራው ለአገራዊ ጥሪዎች በተለይም ወደአገር ቤት ለተደረጉ ታላቅ ጥሪዎችና የህዳሴ ግድብ ድጋፎች ሰፊ ተሳትፎ ከማድረግ ባለፈ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ የተለያዩ አገራትን ባለስልጣኖች በማነጋገርና ሰልፍ በማካሄድ ለኢትዮጵያ ጥብቅና መቆሙን ገልጸዋል።

ዳያስፖራው የውጭ ጣልቃ ገብነትን በመከላከልና የፐብሊክ ዲፕሎማሲ አቅም ሆኖ የአገር ገጽታ ግንባታ ላይ መሳተፉን አድንቀው፤ ወቅታዊና አገራዊ አጀንዳዎችን መነሻ ባደረጉ የማህበራዊ ሚዲያ ዘመቻዎች የዳያስፖራ

የውጭ ተጽዕኖው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







# “የአሸባሪው ሕወሓት የጦርነት ጉሰማ ለመጨረሻ ጊዜ መጥፊያውን የሚያፋጥን ነው”

### -አቶ ሙሉብርሀን ሀይሌ የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ትዴፓ) የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ

**አዲሱ ገረመው**



አዲስ አበባ፡- አሸባሪው ሕወሓት ለሦስተኛ ጊዜ የሚያደርገው ትርጉም አልባ የጦርነት ጉሰማው የመጥፋት እድሜውን የሚያፋጥን ነው ሲሉ የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ትዴፓ) የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ አስታወቁ።

የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ትዴፓ) የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ የሆኑት አቶ ሙሉብርሀን ሀይሌ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አሸባሪው ሕወሓት ለሦስተኛ ዙር ጦርነት እየተዘጋጀ ነው። ይህ የቡድኑ የተለመደው የጥፋት ተግባር ደጋግሞ እየቀጠለ ሲሆን፤ ኢትዮጵያን እኛ ካልመራናት ትፍረስ የሚል ዓላማውን ለማሳካት የትግራይን ህዝብ እንደመያዣ በማድረግ ለማያባራው ጦርነት ህዝቡን እየቀሰቀሰ ይገኛል። የሽብር ቡድኑ የሚያደርገው ትርጉም አልባ የጦርነት ጉሰማው የመጥፋት እድሜውን የሚያፋጥን ነው።

አሸባሪው ሕወሓት የትግራይን ህዝብ ለበርካታ ዓመታት እንደመያዣ አድርጎ ለጦርነት ሲማግደው እንደከረመ አቶ ሙሉብርሀን ገልጸዋል። አሁንም ትርጉም ለሌለው ጦርነት የራሱን ዓላማ ለማሳካት በማይሆን ህልምና ቅዠት አዛውንትና ህጻናትን ሳይቀር ወደ ጦር ግንባር እንዲሄዱ ዳግም ጦርነት ለመቀስቀስ እየንቀሳቀሰ መሆኑን ጠቁመዋል። ይህም የጥፋት ቡድኑን ህልውናውን እንዲያጣ የሚያደርገው ተግባር መሆኑንም ጠቅሰዋል።

አሁን ያለው ለውጥ በኢትዮጵያ ህዝብ ትግል የመጣ ነው ያሉት አቶ ሙሉብርሀን፤ ሕወሓት ለውጡን ለመቀልበስ በርካታ ሙከራዎችን ሲያደርግ መቆየቱን፤ በየምዕራፉ በርካታ ፈተናዎችንና መሰናክሎችን እየፈጠረ የተጀመረው የለውጥ ጉዞ አቅጣጫውን እንዲስት እንዲሁም ኢትዮጵያ እንደትበታተን ሌት ከቀን እየሰራ ያለ ድርጅት መሆኑን ተናግረዋል። ሆኖም ይህ የጦርነት ቅስቀሳ የሽብር ቡድኑ የመጨረሻ የመጥፋት አዝማሚያን

“የአሸባሪው ሕወሓት ... ወደ ገጽ 2 ዞሯል

# በሕገወጥ መንገድ በሚታተሙ ዲጂታል መታወቂያዎች ሕብረተሰቡ እንዳይጭበረበር ጥንቃቄ ሲያደርግ ይገባዋል ተባለ

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- በሕገወጥ መንገድ የተገኙ ዲጂታል መታወቂያዎች በመንግሥት የሚሰጡ አገልግሎቶችን ስለማያስገኙ መታወቂያ እንሠራላችኋለን ከሚሉ አካላት ሕብረተሰቡ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሊያደርግ ይገባዋል ሲል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወሳኝ ኩነት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አሳሰበ።

ከሰሞኑ ዲጂታል መታወቂያዎች በአዲስ አበባ ከተማ በሕገወጥ አካላት ተመሳስለው እየታተሙና እየተሠራጩ መሆኑ በተለያዩ መገናኛ ብዙኃን እየተሠራጨ ይገኛል። መታወቂያዎቹ እስከ 7 ሺህ ብር ድረስ ሲቸበቸቡ እንደነበር ጥናት አደርጌ አገኘሁ የሚሉ መገናኛ ብዙኃን ይፋ አድርገዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ወደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወሳኝ ኩነት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ደውሎ ጉዳዩን ለማጣራት ባደረገው ሙከራ ከኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር ምላሽ አግኝቷል።

በሕገወጥ መንገድ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ዶክተር ታከለ ነጫ



# የቻይና ልማት ባንክ ከኢትዮጵያ ጋር ያለውን ግንኙነት አጠናክሮ ለመቀጠል ዝግጁ መሆኑን ገለጸ

አዲስ አበባ፡- ከኢትዮጵያ ጋር በሁለትዮሽና በባለብዙ ወገን የትብብር ዘርፎች ያለውን ግንኙነት አጠናክሮ ለመቀጠል ዝግጁና ቁርጠኛ መሆኑን የቻይና ልማት ባንክ የአሜሪካና አፍሪካ ዓለም አቀፍ ትብብር ዲፓርትመንት ጄኔራል ኃላፊ ቢያን ሺዩን ገለጹ።

በቤጂንግ የኢትዮጵያ አምባሳደር ተሾመ ቶጋ ከቻይና የልማት ባንክ የአሜሪካና አፍሪካ ዓለም አቀፍ ትብብር ዲፓርትመንት ጄኔራል ኃላፊ ቢያን ሺዩን ጋር ተወያይተዋል።

በውይይቱም በኢትዮጵያና በቻይና ልማት ባንክ መካከል ያለው ትብብር ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ተገልጿል።

የኮቪድ-19 ወረርሽኝና በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የተከሰተው ግጭት በሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳሳደረ እና ኢኮኖሚው ይህን ጫና ተቋቁሞ በማደግ ላይ የሚገኝና ተስፋ ሰጪ ነው ተብሏል።

ባንኩ በሂደት ላይ ላሉ የልማት ፕሮጀክቶችና ለኢትዮጵያ የፋይናንስ ፖሊሲ ተቋማት የሚያደርገውን ድጋፍ እንዲሁም በ8ኛው የቻይና አፍሪካ ትብብር ፎረም የሚኒስትሮች ኮንፈረንስ የልማት ትብብር ግቦች መሰረት ድጋፉን አጠናክሮ እንዲቀጥል አምባሳደር ተሾመ ጥሪ አቅርበዋል።

ባንኩ ከፈረንጆቹ ከ2007 ጀምሮ የኢትዮጵያ ቁልፍ የልማት አጋር ሆኖ የቀጠለ መሆኑን እና የፋይናንስና የልማት ተቋማት ጋርም መልካም ትብብር ያለው መሆኑን የገለጹት ደግሞ ቢያን ሺዩን ናቸው።

ባንኩ ከኢትዮጵያ ጋር በሁለትዮሽና በባለብዙ ወገን የትብብር ዘርፎች ያለውን ግንኙነት አጠናክሮ ለመቀጠል ዝግጁና ቁርጠኛ መሆኑን መግለጻቸውን በቤጂንግ ከኢትዮጵያ ኤምባሲ ያገኘነው መረጃ ያመላክታል።




# ምክር ቤቱ በኢትዮጵያና ቱርክ መካከል የተደረጉ ወታደራዊ ስምምነቶችን አጸደቀ

አዲስ አበባ፡- የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ትላንት ባካሄደው 7ኛ መደበኛ ስብሰባው በኢትዮጵያና ቱርክ መንግሥታት መካከል የተደረገውን የወታደራዊ ማዕቀፍ ስምምነት፣ የወታደራዊ ፋይናንስ ትብብር ስምምነትና የፋይናንስ ድጋፍ ማስፈጸሚያ ፕሮቶኮልን መርምሮ አጸደቀ።

ኢትዮጵያና ቱርክ የወታደራዊ ትብብር ለማድረግ የሚያስችላቸውን የወታደራዊ ማዕቀፍ ስምምነት ነሐሴ 12 ቀን 2013 ዓ.ም በቱርክ አንካራ ከተማ መፈራረማቸው ይታወሳል፡፡

ስምምነቱ በሁለቱ አገሮች መካከል በመከላከያ ዘርፍ የሚደረገው ግንኙነት የሚመራበትን ግልጽ ማዕቀፍ ለመፍጠር ያለመ ነው።

አዋጁ በመከላከያ ኢንዱስትሪ፣ መረጃ ልውውጥ፣ ሎጅስቲክ፣ ጤና አገልግሎት፣ የመረጃ ስርዓትና ሳይበር ጥቃትን መከላከልና በሌሎች ተያያዥ መስኮች ላይ በትብብር ለመስራት የሚያስችሉ ድንጋጌዎችን ያካተተ ነው።

በዚህም የባለሙያዎች፣ የቁሳቁስ፣ የመረጃና የልምድ ልውውጥን በስምምነቱ መሰረት ተግባራዊ ማድረግ ያስችላል።

በተጨማሪ የመከላከያ ትብብር መስኮችን በተመለከተ በሁለቱ አገራት በትምህርትና ስልጠና በተናጠል ወይንም በጋራ በሚዘጋጁ ወታደራዊ ልምምዶች መካፈልን ያስችላል።

ስምምነቱ ኢትዮጵያ የመከላከያ ኢንዱስትሪ ግብዓቶችን፣ የሎጅስቲክ አቅርቦትንና ድጋፎችን እንድታገኝ እንዲሁም በሰው ኃይልና አስተዳደር ዙሪያ ልምድ እንድትቀስም እንደሚያግዝም እንዲሁ፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES' REPRESENTATIVES OF THE FDRE

በተመሳሳይ በኢትዮጵያና ቱርክ መካከል የተደረገው የወታደራዊ ፋይናንስ ትብብር ስምምነት ሁለቱ አገሮች በጋራ ለመስራት የሚያስችላቸው መሆኑ ተገልጿል።

ምክር ቤቱ የፋይናንስ ድጋፍ ማስፈጸሚያ ፕሮቶኮል አዋጆችን ጨምሮ ስምምነቶቹ ለኢትዮጵያ የሚያስገኙትን ጥቅም ላይ በመወያየት በሙሉ ድምጽ አጽድቋቸዋል።

በሌላ በኩል ምክር ቤቱ በኢትዮጵያና በዓለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ መካከል ለገጠር ፋይናንስ ስርዓት ማሻሻያ መርሐ ግብር ለማስፈጸም የተደረገውን የብድር ስምምነት በ3 ተቃውሞ በ8 ድምጸ ታቅቦ በአብላጫ ድምጽ ማጽደቁን ኢዜአ ዘግቧል።



# ኢትዮጵያ ከአጋጠሟት ኢኮኖሚያዊ ችግሮች መውጫ መንገዷ ግብርናውን ማዘመን መሆኑ ተገለጸ

ዳግማዊት ግርማ

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ከአጋጠሟት ኢኮኖሚያዊ ችግሮች መውጫ መንገዷ በግብርናው ዘርፍ ላይ በትኩረት መስራት መሆኑን በዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ ኢኮኖሚክስ ትምህርት ክፍል መምህር የሆኑት ዶክተር ደም መላሽ ሀብቴ ገለጹ።

ዶክተር ደም መላሽ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ በተለይም በኢኮኖሚው ዘርፍ ችግር ውስጥ ትገኛለች፤ ከዚህ ችግር በዘላቂነት ለማውጣት በግብርናው ዘርፍ ላይ ትልቅ ትኩረት ሰጥታ ልትሰራ ይገባታል።

ሥራ አጥነት ፣ የዋጋ ግሽበት፣ የእዳ ጫና፤ የድህረ ጦርነት ችግሮች ፣ የሩሲያና ዩክሬን ጦርነት፣ የኮቪድ 19 ወረርሽኝ እንዲሁም ፈጣን የህዝብ ዕድገት በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ ትልቅ አሉታዊ ጥላቸውን መጣላታቸውን የጠቆሙት ዶክተር ደምመላሽ፤ እነዚንና መሰል ተግዳሮቶችን ለማለፍ ኢትዮጵያ ግብርናን እንደ ዋንኛ መፍትሄ በመቀበል ብዙ ሥራዎች መስራት እንደሚጠበቅባትም አመልክተዋል።

እንደ ዶክተር ደም መላሽ ገለጻ፤ኢትዮጵያ ግብርናው ዘመናዊ የሚሆንበትን መንገድ ያለመድከም መስራት ያስፈልጋል። ዘርፉን ዘመናዊ ማድረግና የወቅቱን ችግር ማለፍያ መንገድ አድርጎ መጠቀም ለነገ የማይባል ሥራ ነው።

ኢትዮጵያ በወጪ ንግድ የተወሰኑ የግብርና ምርቶች ላይ ያገኘችው ገቢ ጥሩና አበረታች መሆኑን የገለፁት ዶክተር ደምመላሽ፤ በተገኘው መልካም ውጤት ሳይዘናጉ ቀጣይነት ያለው ሥራ መስራት እንደሚገባም ተናግረዋል።

ከአውሮፓውያኑ እኤአ ከ1980ዎቹ ጀምሮ ግብርና መር ኢንዱስትሪ ላይ ትኩረትን አድርገው መስራታቸውን ያመላከቱት ዶክተር ደም መላሽ፤ በዚህ አሰራር ውጤታማ ሁነዋል። ለኢትዮጵያም አሁናዊ ሁኔታ እድገትን ከገጠር ልማት ጋር የተቀናጀ አድርጎ መስራት በኢኮኖሚው ዘርፍ ለሚስተዋሉ ችግሮች ሁሉ ቁልፍ መፍትሄ መሆን እንደሚችልም ገልጸዋል።

አርሶ አደሮች ቴክኖሎጂዎችን የመጠቀም አቅማቸውን በማጎልበት የግብርና ምርትና ምርታማነት የማሳደግ ሥራን ማስቀጠል እና የዘርፉን ተዋንያን የማበረታታት ተግባር በትኩረት መፈጸም እንደሚገባም ገልፀዋል።

ዶክተር ደምመላሽ 80 በመቶ የሆነው የሀገራችን ህዝብ ኑሮውን ከግብርና እና ተያያዥነት ባለው ጉዳዮች እንደሚገፋ አመልክተው፤አሁንም ገበሬዎች በባህላዊ መንገድ በማረስ ላይ መገኘታቸው ዘርፉን በብዙ እንደጎዳው በመግለፅ መንግሥትም ሆነ የሚመለከታቸው አካላት ግብርናውን በማዘመን ረገድ ትኩረት እንዲሰጡ ጥሪቸውን አስተላልፈዋል፡፡




# ኢትዮጵያና ፈረንሳይ የ1 ነጥብ 2 ቢሊየን ብር የዕርዳታ ስምምነት ተፈራረሙ

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያና የፈረንሳይ መንግሥታት የ1 ነጥብ 2 ቢሊየን ብር የዕርዳታ ስምምነት ተፈራረሙ።

የገንዘብ ድጋፉ የፈረንሳይ መንግሥት በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚከናወኑ ሶስት የተለያዩ ፕሮጀክቶች የሚውል መሆኑ ተገልጿል።

የመጀመሪያው ፕሮጀክት፣ በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ ታሪካዊ ቅርሶችን ጥገና እና ክብካቤ ሥራ ሲሆን፣ ቅርሶቹ ለጎብኚ ምቹና ሳቢ እንዲሆኑ የሚያስችል ነው ተብሏል።

ሁለተኛው ፕሮጀክት ደግሞ የኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ኃይል የሚያስገነባውን የስልጠና ተቋም ግንባታና የውስጥ መገልገያ መሳሪያዎች የማሟላት ሥራ መሆኑን የገንዘብ ሚኒስቴር መረጃ ያመላክታል።

ሦስተኛው፣ በኢትዮጵያ የሲቪል ማኅበራት ኤጀንሲ ድጋፍ ነው ተብሏል።

ስምምነቱን የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታ ሰመሬታ ሰዋሰው እና በኢትዮጵያ የፈረንሳይ ልማት ድርጅት ኃላፊ ቫሌሪ ቲኦዎ በኢትዮጵያ የፈረንሳይ አምባሳደር ሬሚ ማሬሾ በተገኙበት ተፈርሟል።

# ዜጎች ለእያንዳንዱ አገራዊ ችግሮች የመፍትሄው አካል መሆን እንደሚጠበቅባቸው ተገለጸ

*- ሚዲያዎች እየተበራከቱ የመጡ የሀሰት መረጃዎችን ማጋለጥ ይኖርባቸዋል*

አዲስ አበባ፡- ዜጎች ሃይማኖትና ብሄር ተኮር በሆኑ አፍራሽ ቅስቀሳዎች ሰለባና መሳሪያ መሆን እንደሌለባቸው ተገለጸ።ሚዲያዎች እየተበራከቱ የመጡትን የሀሰት መረጃዎችን ማጋለጥና ህብረተሰቡን ማስገንዘብ እንደሚኖርባቸውም ተጠቁሟል።



የአዲስ አበባ አስተዳደር ባህል፣ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ሂሩት ካሳው "የዜጎች ቀጥተኛ ሚና ለሁለንተናዊ ብልጽግና» በሚል ትናንትን ከኪነ ጥበብና ሚዲያ ባለሙያዎች ጋር በተካሄደው ውይይት እንደገለጹት፤ዜጎች ለእያንዳንዱ አገራዊ ችግሮች የመፍትሄው አካል ለመሆን በንቃት መሳተፍ ይጠበቅባቸዋል።

የኑሮ ውድነት፣የሥራ አጥነት፤ሌብነትና የሰላም ችግር የአገራችን ያልተሻገርናቸው ፈተናዎች ናቸው ያሉት የቢሮ ኃላፊዋ፤እነዚህን ችግሮች ለመፍታት መንግሥት የሚያደርገው ሁለንተናዊ ጥረት እንደተጠበቀ ሆኖ ዜጎችም ተሳትፎአቸውን ማጎልበት እንደሚኖርባቸውም ተናግረዋል።

ዶክተር ሂሩት፤አገራዊ ለውጡ በመላው ኢትዮጵያውያን ትግል እንደመጣው ሁሉ አገራዊ ብልጽግና ለማምጣትም የእያንዳንዱ ዜጋ ተሳትፎና ተግባራዊ እንቅስቃሴ ወሳኝና አስፈላጊ ነው ብለዋል።

የኢትዮጵያን ሰላምና አንድነትን የማይፈልጉ ኃይሎች በሃይማኖትና በብሄር ሽፋን በህዝቦች መሀከል መራራቅንና ጥላቻን የሚፈጥሩ የሀሰት መረጃዎች እያሰራጩ መሆናቸውን ጠቁመው፤ ሁሉም የአገሪቱ ዜጎች ሆነ የከተማዋ ነዋሪ እነዚህ አፍራሽና ግጭት ቀስቃሽ ሀሳቦችን ካለመቀበል ጀምሮ መታገልና ማጋለጥ እንደሚኖርበት አስገንዝበዋል።

መንግሥታትን ጨቋኝ ናቸው፣ ገዳይ ናቸው ፣ደካማ ናቸው፣አይሰሩም ብሎ መተቸት ቀላልና እውቀት የማይፈልግ ነው ያሉት አርቲስት ደበበ ሰይፉ ፤ዕውቀት የሚሆነው መልካሙንና ክፉውን ለይቶ መልካሙን ማስፋትና ችግሩን መታገል ሲቻል መሆኑን ተናግረዋል።

በተለይ ሚዲያዎችና የኪነ ጥበብ ዘርፉ የሚጠበቅባቸውን አገራዊ ኃላፊነት በብቃት እንዲወጡም በዚህ ዘርፍ የሚመደቡ ኃላፊዎች ኃላፊነታቸውን በአግባቡ የሚወጡ መሆን እንዳለባቸው ጠቁመው፤ባለሙያዎችም ሙያቸውን ለማሳደግ ፍላጎቱና ዝግጁነቱ ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል ብለዋል።

መንግሥትም የዜጎችን አንድነት፣መግባባትና አብሮነት የማጠናከር ሥራ የመጀመሪያው ተግባር መሆን እንደሚኖርበትም ጠቁመዋል።

ከሙዚቀኞችና ከፊልም ፕሮዲሰሮች ማህበራት ተወክለው የመጡት አቶ ፋንታው ቸኮልና አቶ ሰለሞን ታፈሰ እንደገለጹት፤የኑሮ ውድነት፣ሌብነት፣ዘረኝነት፣የመሬት ወረራና የሰላም እጦት አገራዊ ችግሮች ናቸው።መንግሥት እነዚህን ችግሮች ለመፍታት የሚያደርገውን ጥረት በየጊዜው ለህዝቡ ማሳወቅ አለበት።ህዝቡም የሚጠበቅበትን ሚና ለመወጣት ዝግጁ ይሆናል ።



"አርአያ ሁናችሁ ምሩን" ያሉት አቶ ፈንታው፤ የመንግሥት አመራር የመልካም ነገሮች አርአያ መሆን ካልቻለ ነገ ሀገር ተረካቢ ትውልድ ለማፍራት እንደማይቻል ተናግረዋል።

በውይይት መድረኩ በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ሰላም ለማደፍረስ በተቀናጀ መልኩ በሃይማኖትና በብሄር ሽፋን የሀሰት አካውንቶች በመክፈት አፍራሽ መልዕክቶችን በማሰራጨት የህዝቡን አብሮነት ለማላላት ጥረት እየተደረገ መሆኑ ተጠቁሞ በማህበራዊ ሚዲያ የሚተላለፉ አፍራሽ መልዕክቶችን ካለመቀበል ጀምሮ ማክሸፍና መታገል ኢትዮጵያዊ ነኝ ከሚልና አገሩን ከሚወድ ዜጋ ሁሉ እንደሚጠበቅ ከተወያዮቹ ተገልጿል።

የማህበራዊ ሚዲያ አንቂዎች፣መደበኛ ሚዲያዎችና የኪነ ጥበብ ባለሙያዎችም የሀሰት መረጃዎችን በማጋለጥና ዜጎች ለሁለንተናዊ አገራዊ ብልጽግና የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉ በማስገንዘብና መረጃ በመስጠት የሚጠበቅባቸውን ሚና እንዲወጡ ጥሪ ቀርቧል።

## የውጭ ተጽዕኖው...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ማህበረሰብ አባላት የNo more /የበቃ!/ እንቅስቃሴን በውጤታማነት በማስተባበር ሚናቸውን ለተወጡ ኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያን ዳያስፖራዎች ምስጋና አቅርበዋል።

ከዚህ ጥረት ባለፈ የውጭ ምንዛሪ ፍሰትን ለመጨመር ዳያስፖራው በሕጋዊ መንገድ ወደአገሩ ገንዘብ እንዲልክ በተደረገው ክትትልና ድጋፍ በዘጠኝ ወሩ ሶስት ነጥብ ሶስት ቢሊዮን ዶላር መላኩን አስታውቀዋል።

ባለፉት ዘጠኝ ወራት 97 ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር ካፒታል ያስመዘገቡ ዳያስፖራዎች ወደኢንቨስትመንት መግባታቸውን ጠቁመው፤ ዳያስፖራው ለመከላከያ ሰራዊትና ለህልውና ዘመቻው፣ ለበጎ አድራጎት ሥራዎችና በልዩ ልዩ ገቢ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች በድምሩ 263 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ብር በማሰባሰብ ለአገሩ አለኝታ መሆኑን ማረጋገጡን ገልጸዋል።

ከዳያስፖራው ባለፈ አገር ውስጥ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንም አንድነታቸውን በማጠናከርና ሰላማቸውን በማስጠበቅ የዲፕሎማሲ ሥራው ውጤታማ እንዲሆን የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ ጥሪ አቅርበዋል።

የአገር ሰላምና አንድነት ሲጠናከር በቀጠናዊ ጉዳዮች ላይም የተቀናጀ ሥራ ማከናወን እንችላለን። ወደቀጣናው ብናተኩር በጂኦፖለቲካል ፍላጎትና በልዩ ልዩ ውስጣዊና ቀጣናዊ ሁኔታዎች ዲፕሎማሲያችን የበለጠ ተጽዕኖ ፈጣሪና ቀድሞ መንቀሳቀስ የሚፈልግበት ዘመን ላይ እንገኛለን ብለዋል።

ከዚህ አኳያ ብሔራዊ ጥቅማችንን ለማስከበር ተደማጭነታችንን ለማሳደግና ተደራሽነታችንን ለማስፋት ካለፉት ዓመታት ልምዶችና ዘመኑ የሚጠይቀውን ተልዕኮ መነሻ ያደረገ ተቋማዊ የለውጥ ስርዓት ተግባራዊ መሆን ጀምሯል ሲሉ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ ከጎረቤት አገሮች ጋር መልካም ግንኙነት አላት ያሉት አቶ ደመቀ፤ ከኤርትራ ጋር የጋራ ጥቅሞቻችንን መሰረት በማድረግ በትብብር እየሰራን እንገኛለን። ግንኙነቱን ወደ ጠንካራ የኢኮኖሚ ትብብር ለማሸጋገር የተለያዩ ተግባራት እየተከናወኑ መሆኑን ጠቁመዋል።

የድንበር አካባቢ ንግድ የሚያሳድጉ የመሰረተ ልማት ግንባታዎች፣ የወደብ አጠቃቀም፣ የጉምሩክና የኢሚግሬሽን እንዲሁም የሁለቱን አገራት ህዝቦች ተጠቃሚ ሊያደርጉ የሚችሉ የትብብር ማዕቀፎችን ለማበጀት ትኩረት ሰጥተን እየሰራን እንገኛለን" ብለዋል።

በተመሳሳይም ከጂቡቲ፣ ኬንያ፣ ሶማሌያና ሌሎቹም ጎረቤት አገራት ጋር በትብብር በመስራት የሚነሱ ችግሮችን ለማፍታትና የንግድ፣ የሰላምና ደህንነት እንዲሁም የሕዝብ ለህዝብ ግንኙነቶችን ለማጠናከር ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዘርፈ ብዙ ጥረቶችን እያደረገ መሆኑን አስታውቀዋል።

በሌላ በኩል የአፍሪካ አገራት፣ ሩሲያ፣ ቻይና ህንድና ሌሎች ወዳጅ አገራት ኢትዮጵያ ችግር ውስጥ በነበረችበው ወቅት ሁሉ ያለማወላወል በዓለም አቀፍ መድረኮች ላሳዩት ድጋፍ አቶ ደመቀ መኮንን ምስጋና አቅርበዋል።

## በሕገወጥ መንገድ በሚታተሙ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወሳኝ ኩነት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ታከለ ነጫ፤ ዲጂታል መታወቂያዎቹ በሕገ ወጥ መንገድ መታተማቸውን አምነው እንዲያውም ከተጠቀሰው ዋጋ በላይ መሸጣቸው እንደተደረሰበት ገልፀዋል። ሆኖም የሚሸጡት መታወቂያዎች መለያ ኮድ ወደ መንግሥትም ሆነ ወደ ኤጀንሲው ቋት ያልገቡ በመሆናቸው መንግሥታዊ አገልግሎት ለማግኘት የማያስችሉ ተራ ወረቀቶች ናቸው ብለዋል።

ምንም እንኳን በማጭበርበር የተገኙት መታወቂያዎች ከመደበኛው ጋር ቢመሳሰሉም መለያ ቁጥራቸው ወደ ተቋሙ ቋት ስለማይገቡ ከመንግሥት ተቋማት አገልግሎት ለማግኘት የሚያስችሉ አይደሉም።ኅብረተሰቡ ከዚህን መሰል ድርጊት ራሱን እንዲቆጥብ መክረዋል።

ኤጀንሲው ከዚህ ቀደም እንደሚያደርገው ሁሉ ችግሩን ለመከላከል ከፀጥታ አካላት እና ከሌሎች መዋቅሮች ጋር በትብብር እየሠራ እንደሚገኝ ዋና ዳይሬክተሩ ጠቁመዋል። በዚህም ዲጂታል መታወቂያ እንሠራላችኋለን በማለት ሲያጭበረብሩ እጅ ከፈንጅ የተያዙ የወሳኝ ኩነት ምዝገባና አስተዳደር ሠራተኞችን ጨምሮ ሌሎች በጉዳዩ የተሳተፉ አካላት በቁጥጥር ሥር ውለዋል ብለዋል። እስካሁን በተደረጉ ክትትሎች ከ11 በላይ ሰዎች ተይዘዋል።

የተቋሙ ሠራተኞች እንደ ሠሩት ሥራ ክብደትና ቅለት የደመወዝ ቅጣት፣ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያና የመሳሰሉ እርምጃዎች መወሰዳቸውንና ከመሥሪያ ቤቱ ውጪ ይህን ሥራ ሲሠሩ እጅ ከፈንጅ በፖሊስ ተይዘው ጉዳያቸው በፍርድ ቤት እየታዩ የሚገኙ እንዳሉ ዳይሬክተሩ ገልፀዋል።

በተጨማሪም የኤጀንሲው ሠራተኞች ሆነው አስፈላጊውን መረጃ ላላሟሉ አገልግሎት ፈላጊ ዜጎች የልደት እና መሰል ሰርተፍኬት የሚሰጡ ሠራተኞች ከደመወዝ ቅጣት እስከ መጨረሻ ማስጠንቀቂያ በሚደርስ ቅጣት ተቀጥተዋል ተብሏል።

በተጭበረበረ መንገድ መታወቂያ ያወጡ ሰዎች ወደ መንግሥት ተቋማት ሄደው አገልግሎት ለማግኘት በሚሞክሩበት ጊዜ መለያ ቁጥራቸው አይሠራም ያሉት ዶክተር ታከለ፤ ይህን ዓይነት ነገር በሚገጥም ጊዜ ግለሰቦቹ በፖሊስ እንዲያዙ በማድረግ መታወቂያውን ያገኙበት መንገድ እንዲጣራ ተደርጎ ሁለቱም አካላት እንዲቀጡ ይደረጋል ተብሏል።

ማንኛውም አካል በተጭበረበረ በተገኘ መታወቂያ ከመንግሥት ሊያገኝ የሚገባውን አገልግሎት ስለማያገኝ ገንዘቡን አውጥቶ ለአጭበርባሪዎች አይጋለጥ ያሉት ዶክተር ታከለ እንደዚህ መሰል ነገሮች ሲያጋጥሙም 7533 ነፃ የጥቆማ የስልክ መሥመር ላይ ጥቆማ እንዲሰጥ ጠይቀዋል።

## "የአሸባሪው ሕወሓት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ያሳያል ብለዋል።

አቶ ሙሉብርሀን፤ የሽብር ቡድኑ ባለፈው ጦርነት በአፋርና አማራ ክልል ወረራዎችን በማድረግ በርካታ ጥፋቶችን እንደፈጸመ አስታውሰዋል። ህዝቡንም ወደ ጦርነት በማስገባት ብዙ መስዋእትነት ማስከፈሉን ገልጸው፤ የትግራይ ህዝብ በጦርነቱ እንደማይጠቀምና ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር ተለያይቶ መኖር የማይችል እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል ብለዋል።

"በጦርነት የሚመጣ ትርፍ የለም። የሽብር ቡድኑ ዓላማ ትግራዊያን የሌሏትን ትግራይን ለመፍጠር ነው። ትግራዊያንን ለመጨረስና ለማጥፋት ካልሆነ በስተቀር ጦርነቱ ምንም ዓይነት ትርጉም የለውም።የኢትዮጵያ ብልጽግናና ትንሳኤ የሚረጋገጠው በአሸባሪው በሕወሓት መቃብር ላይ ነው" ሲሉም ተናግረዋል።

የሽብር ቡድኑ ከግጭት ውጭ መኖር ስለማይችል ግጭትን ለመፍጠር ዳግም እየተንቀሰቀሰ ነው ያሉት አቶ ሙሉብርሃን ፤ ቡድኑ የከሰረና የማይድን በመሆኑ፤ የትግራይ ህዝብና የትግራይ ወጣት የማይድን ህመም በማስታመም መክፈል የማይገባውን ዋጋ እየከፈለ መቆየት የለበትም ሲሉም መክረዋል። ህዝቡ ይሄን በመረዳት በጦርነት ተሳታፊ እንዳይሆንም ነው ጥሪ ያቀረቡት።

ህዝቡ ከአጎራባች ክልሎች ጋር ነግዶና ሰርቶ በሠላም እንዳይኖር ችግር ውስጥ የከተተው ይህ ኃይል በመሆኑ፤ በተቻለ መጠን ይህን ኃይል የታጠቁትም ሆኑ ያልታጠቁ ትግራውያን ሊዋጉትና ሊያስወግዱት እንደሚገባ አስገንዝበዋል። ሕወሓት ካልጠፋ የትግራይ ህዝብ ሠላም ስቃይና መከራ ሊያቆም ስለማይችል እንዲወገድ መታገል አለባቸው ነው ያሉት።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ርዳታ እያደናቀፈና፤ የትግራይን ሕዝብ በጦርነት እየማገደ ያለው አሸባሪው ሕወሓት ዛሬም የትግራይ ሕዝብ ጠላት ነው!

አሸባሪው ሕወሓት ዛሬም የትግራይን ህዝብ ነጻ አወጣለሁ፣ ለትግራይ ህዝብ ቆሜያለሁ የሚለውን ዲስኩር ቀጥሎበታል። ይሁን እንጂ የትግራይ ህዝብ ስቃይና መከራ እንዳይቆም ፤ ህዝቡ ተረጋግቶ ወደ መደበኛ ኑሮው እንዳይመለስ ለሶስተኛ ዙር ጦርነት እየጎሰመ ይገኛል። የጥላቻና የበሬ ወለደ ፕሮፓጋንዳውን በመንዛትም ጭምር የትግራይን ሕዝብ ዳግም በጦርነት ለማስጨረስ ቅስቀሳ እያደረገ ይገኛል።

አሸባሪው ሕወሓት በሕዝቡ እንቢተኝነት ከስልጣኑ ተፈናቅሎ ወደ ትግራይ ከመሸገ ጀምሮ የትግራይን ሕዝብ በተለያየ መልኩ እያሰቃየ ነው። በዚሁ አሸባሪ ቡድን የተነሳ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ህዝቡ ስቃዩን እየበላ ይገኛል።

አብሮ ተጋብቶና ተዛምዶ በፍቅር ከኖረው የአማራና የአፋር ክልል ህዝቦች ፤አንድ ቋንቋ ተናጋሪ እና አንድ ባህል ተጋሪ ከሆነው የኤርትራ ወንድምና እህቱ ጋር ተከበህል ፤ የዘር ማጥፋት ሊፈጸምብህ ነው በሚል የሀሰት ወሬ ሕዝቡን ወደ ጦርነት ሲዳርገው ቆይቷል።

እድሜያቸው ለውትድርና ያልደረሱ ህፃናትና ታዳጊዎች ደብተር ይዘው ወደ ትምህርት ቤት ሳይሆን ነፍጥ ይዘው ለጦርነት እንዲሰለፉ አድርጓቸዋል። ባላመኑበትና በማያውቁት ከእህት ከወንድማቸው ጋር እንዲዋጉ አላስፈላጊ መስዋዕትነት እንዲከፍሉ አስገድደውታል።

እናቶች ለፍተውና ደክመው ያሳደጓቸውን ልጆቻቸውን አስተምረው ፣ አስመርቀውና ድረው ወግ ማዕረግ እንዲያዩ ሳይሆን ለጦርነት ገብረው የወላድ መካን እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። ዛሬም የትግራይ እናቶች ልጆቻችን የታሉ የሚለውን ጥያቄ ከመጠየቅ አልቦዘኑም። እንባቸውን ከጉንጫቸው አላበሱም። አሁንም የረሀብና የሰቆቃ ኑሮን ከመግፋት አልዳኑም። ይባስ ብሎ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ በችግራቸው ላይ የከፋውን የጦርነት ድግስ እየደገሰላቸው ነው። ወደው ሳይሆን ተገደው ሴት ወንድ ሳይሉ አምራቹ ሁሉ ለጦርነት እንዲሰለፍ አሸባሪው ሕወሓት ቅስቀሳውን ቀጥሏል። እምቢ አሻፈረኝ ያለውን በማስፈራራት ፣ የእርዳታ ምግብ በመንፈግ ጭምር መከራውን እያበላው ይገኛል።

አሸባሪው ሕወሓት አሁንም ከአጥፊ ተግባሩ የማይማር፣ ለህዝብም ሆነ ለሀገር የማያስብ በመሆኑ እንጂ ለትግራይ ህዝብ የቆመ ቢሆን ኑሮ አሁን ወቅቱ የእርሻ በመሆኑ ሕዝቡ ፊቱን ወደ እርሻ ሥራው እንዲያዞር ባደረገ ነበር። የአምናውና የካቻምና እርሻ አለመ ታረስ ምን ያህል በችግር ውስጥ እንዲማቅቅ እንዳደረገው የትግራይ ሕዝብ ራሱ ምስክር ነው። ለቀጣዩ ዓመትም ይሄንኑ የስቃይ ኑሮ እንዲገፋ ተፈርዶበታል።

ዛሬም አሸባሪው ሕወሓት ከአጥፊ ድርጊቱ ሳይጸጸት ለሶስተኛ ዙር ጦርነት ህዝቡን እየቀሰቀሰና የሞት ድግሱን ለማፋጠን በየመገናኛ ብዙኃን እየፎከረ ይገኛል። ይሄ ሀገርና ሕዝብ ጠል የሆነ አሸባሪ ቡድን ለትግራይ ህዝብ አሳቢ ሳይሆን ጠላት መሆኑን ከድርጊቱ ማረጋገጥ ይቻላል። የትግራይ ህዝብ መከራውን አይቶ በችግር ተጠብሶ በሴፍቲኔት ድጎማ ካሳደጋቸው ልጆቹ ጥቂቱ እንኳን እንዳይተርፍ አሁንም ከ60 ዓመት በታች ዕድሜ ያለው ማረስና ቤተሰብን መመገብ የሚችለውን አምራች ኃይል በሙሉ በጠላት ተከበናል እያለ የጦርነት ነጋሪቱን ይጎስማል።

በችግር የተቆራመደው የትግራይ ሕዝብ ምግብ፣ መድኃኒትና ሌሎች እርዳታዎች እንዳይገቡለት መንገድ በመዝጋት ከብዙ ችግርና ተጽእኖ ምክንያት እርዳታው ቢገባም እርዳታውን ይዘው የገቡ መኪኖች እንዳይወጡ እርዳታ የማጓጓዙ ሥራም እንዳይሳለጥ እንቅፋት ሆኗል።

መንግሥትና ለትግራይ ህዝብ ምግብ፣ መድኃኒት ፣ ነዳጅ እንዲሁም ገንዘብ በበቂ ሁኔታ እንዲገባ ያላሰለሰ ጥረት እያደረገ ይገኛል። በተቻለ መጠን አሁንም መጠነ ሰፊ ምግብ፣ መድኃኒት ፣ ገንዘብና ሌላውም እየገባ ነው።

ይሁን እንጂ አሸባሪው ሕወሓት አሁንም እንደከዚህ ቀደሙ ሁሉ እርዳታውን ለሕዝቡ ሳይሆን በጦርነቱ ሊማግደው ለሚያዘጋጀው ኃይል ቀለብና ልጁን ለጦሩነቱ አሳልፎ ለሰጠ ወላጅ ብቻ ድጎማ እያደረገው ነው። ይሄን የአሸባሪው ሕወሓት ሴራ ችግሩ እየተፈራረቀበት ያለው የትግራይ ህዝብ በቃ ሊለው ይገባል። ለሶስተኛው ዙር ጦርነት ልጁን ለእልቂት ከመዳረጉ በፊት እንቢ አሻፈረኝ ማለትም አለበት። የትግራይ ሕዝብ ጠላቱ አጎራባች ክልሎችና ኤርትራ ያለው ህዝብ ሳይሆን ራሱ አሸባሪው የሕወሓት ቡድን መሆኑን ሊረዳ ይገባል ።

አሸባሪው ሕወሓት ለትግራይ ህዝብ መቆሙን የሚያስመሰክረው እናትን ካለ ልጅ በማስቀረት፣ ህጻናትና ሴቶችን በማስራብና በማስደፈር ፣ ክልሉን የጦርነት መነሰሚያ በማድረግና ለክልሉ ህዝቡ በየአቅጣጫው ጠላት በማፍራት እንዲሁም እርዳታ እንዳይገባ በማድረግ አይደለም።

ለሕዝብ ቢያስብ ርዳታውን አስገብቶ ለሁሉም በፍትሀዊ መንገድ እንዲከፋፈል በማድረግ ከረሀቡ በታደገው ነበር። ለሕዝብ ቢያስብ ጉልበት ያለው ሊሰራ የሚችለው ነዋሪ ሁሉ ወደ እርሻ ሥራ እንዲሰማራ ባደረገም ነበር። ሕዝቡ ከእህት ከወንድሙ ጋር በይቅርታ ተላልፎ ሰላማዊ ኑሮውን እንዲመራ ባደረገም ነበር። ነገር ግን እውነታው ለትግራይ ሕዝብ ያለ ፍቅር ሳይሆን የስልጣን ጥመኝነት ነው። ሕዝብ አልቆ አሸናፊ እሆናለሁ፣ ትግራይን እገነጥላለሁ ፤ አገር አፈርሳለሁ የሚል የቁም ቅዠት ነው። በመሆኑም ይሄን አሸባሪ ቡድን የትግራይ ሕዝብ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በቃህ ሊለው ይገባል።


ኢፕድ

አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ዋና አዘጋጅ

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73

ፋክስ 011-126-58-12

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

**ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::**

# “የጦቢያዋ — ምስራቅ ተረፈ - ሀ...ግእዝ፣ ሁ... ካዕብ ..!!

ከአስባቸው ደሳለኝ አበሻ (ለንደን)

ግጥም የስነ ውበት ምስጢር በመሆኑ ስሜታዊ ግንዛቤን የሚመረምር የፍልስፍና ዘርፍ ነው ይላሉ ሊቃውንቶቹ። ለኔ ግን የንስሀ ፀሎት ይመስለኛል። ምክንያቱም ጥበብ እንደ ተገለፀ ቅርፅና ፅንሰ-ሀሳብ መኖሩ ውስብስብ ታሪክ ቢኖረውም ከጥንት ጀምሮ እስከ ሰው ልጅ የፍፃሜ ታሪክ ድረስ ስነ መለኮታዊ ኃይል አለው ብለው ከሚያምኑት አንዱ በመሆኔ የሀጢአትን እድፍ ለማፅዳት ከነፍስ አባት ጋር የሚደረግ ሚስጥራዊ ኑዛዜ ሆኖ ይሰማኛል።

እንደ ዓለማዊ ስናስበው ደግሞ ያንድን ነገር ጥቅምና ጉዳቱን አመዛዝኖና መስጥሮ ቢሻው በዜማ ካልሆነም በእንጉርጉሮ የነገሮችን ስብጥርና ቅላፄ ከሽኖና ምጥን አርጎ በመጭመቅ ከአንድ አረፍተ ነገር ተነስቶ ብዙ ሺህ ሕልሞችን መፍታት የሚችል ኃይል እንዳለው የስነግጥም ሃያሲያን ቃላቸውን ሰተውለታል። ከዚህ አኳያ፣ የሥነ ውበት ፈላስፋዎች አጥብቀው የሚያጠያይቁትም ሰዎች ምን መስማት፣ ማየት፣ ማሽተት፣ መንካት እና መቅመስ እንደሚወዱ ከገጣሚው አዕምሮ የሚፈልቁትን ሚስጥረ ሐሳቦችን ታዳሚውን በኀዘንና በትካዜ፣ በሳቅና በደስታ ማማለላቸውን ከመመርመርመርና ከመግለፃቸው ባሻገር፤ የጥበብ ፍልስፍና የውበት፣ የተፈጥሮ እና የፍጥረት ውስጣዊ እና ውጫዊ ግንኙነትን መለኪያ ሚዛን አድርገው ወስደውታል::

ስለዚህ ገጣሚዎች ስለ ሩቁ ታሪካዊ ዘመን፣ ስለ ሰዎች፣ ፍጹም የተለየ የአኗኗር ዘይቤ ሊናገሩ ይችላሉ:: ቁምነገሩ ገጣሚዎቹ ሁል ጊዜ የሚሰማቸው ስሜቶች አሁን ላለው አድማጭም ሆነ አንባቢ እንዴት እንደተረዱት በምናባቸው በፈጠሩት ውብ ዓለም አካል የሆነውን ሕይወታችንን ለማጣጣም መሞከራቸውን አድናቂ ነኝ::

ለዛሬው ስለ ስነግጥም ባለችኝ ዕሩብ የማትሞላ እውቀቴ ይሀን ያክል ካሉኩኝ ይብቃኝና ወደ ርዕሴ ልመለስ። እአአ 14/ 5/2022 ቅዳሜ በለንደን ሰዓት አቆጣጠር ከቀኑ 5 ሰዓት ጀምሮ ታላቅ የግጥም ምሽት ለመከታተል ኖርዝ ለንደን ቾክ ፋርም በአንድ ኮሌጅ አዳራሽ ውስጥ ተገኝቼ ነበር። ምስራቅ ተረፈና ዶክተር በድሉ ዋቅጅራ እንዲሁም ትዕግስት ማሞ ለስሜት ተፈላጊ የሆኑ ውበት አላቸው የሚባሉ ምርጥ የስነ ግጥም ሥራዎቻቸውን አቅርበው ሳዳምጥ አንድ ነገር ትኩረቴን ሳበው::

**ስለዚህ ገጣሚዎች ስለ ሩቁ ታሪካዊ ዘመን፣ ስለ ሰዎች፣ ፍጹም የተለየ የአኗኗር ዘይቤ ሊናገሩ ይችላሉ:: ቁምነገሩ ገጣሚዎቹ ሁል ጊዜ የሚሰማቸው ስሜቶች አሁን ላለው አድማጭም ሆነ አንባቢ እንዴት እንደተረዱት በምናባቸው በፈጠሩት ውብ ዓለም አካል የሆነውን ሕይወታችንን ለማጣጣም መሞከራቸውን አድናቂ ነኝ::**

ለካስ ውበት ከተፈጥሮ ብቻ ሳይሆን ከሰው ሥራም ይመነጫል። በሰው ልጅ ጎሊና ውስጥ የሚመላለሱ እንደዚህ አይነት ቁም ነገሮች ሲነበቡ ማድመጥ ምን ያህል ሊያስደስት እንደሚችል በዚህ ክፉ ዘመን ላለን ትውልዶች አንድ እውነት አስጨብጠውናል። ምክንያቱም ይህ እውነት የተከናወነውና ከግጥማቸው ስንኞች የተደመጡ ሃሳቦች ያስተጋቡት በኪነ ጥበብ ልሳን የፍቅርን አሸናፊነት ነው:: እኔም በሰማሁት ደስተኛ ከመሆኔም በላይ በሀሳባቸው እስማማለሁ።

በፕሮግራሙም ላይ የቀረቡት ሶስቱ ገጣሚዎች የራሳቸውን ፈጠራና ለእይታ ቅርብ ያደረጋቸውን የስነ ጥበብ ምአዛቸውን የሰው ልጅ ደስታን እንዲያጎናፅፍ አድርገው ከማቅረባቸውም ባሻገር፤ ይሄን የፍቅርን አሸናፊነት ከፍ ያደረገ ጥበባቸውን ያሳረፉበት ለትውልድ የሚተርፍ የግጥም መደብል ፅፈው አበርክተውልን ገዝተን አስፈርመናል::

ታዲያ አበጃችሁ ብዕራችሁ አይንጠፍ ማለት ተገቢ በመሆኑ ለሶስቱም አድናቆቴ ይድረስልኝ:: በኔ በኩል ስለ እያንዳንቸው ብቃት ብፅፍ ደስ ባለኝ ነበር:: ነገር ግን ሌላ አስቸኳይ ጉዳይ ገጥሞኝ ፕሮግራሙን ሳልጨርስ ወጣሁ:: እስከ ነበርኩበት ሰዓት ግን የተሰማኝን አንድ ነገር ብቻ ማለት እፈልጋለሁ። እንደምታውቁት በአንድ ጊዜ ሁሉንም የዓለም ሙዚየሞች መጎብኘት አይቻልም፤ ሁሉንም ሲምፎኒዎች፣ ሶናታስ፣ ኦፔራዎችን ማዳመጥ አይችልም። ሁሉንም የስነ-ህንፃ ዋና ሥራዎችን መገምገም አይችልም። ሁሉንም ግጥሞች እንደገና ማሰላሰል አይችሉም፤ እናም ከሁሉም ዓይነት ውስጥ አንድ ሰው ለነፍሱ በጣም ቅርብ የሆነውን ነገር ይመርጣል። ይህም ለአእምሮው እና ለስሜቱ ማረፊያ የሚመርጠው ነው:: ለኔም የነፍስ ማረፊያ ሆና ብዕሬን እንዳነሰ የገፋፋችኝ “የጦቢዋ “ ምስራቅ ተረፈ ያቀረበቻቸው ስነ ግጥሞች የፍቅር ሰቆቃና ሐያልነት የያዙ ርዕሰ ጉዳዮች ስለነበሩ ትኩረቴን ስበው ከሷ ጋር አብሬ አቆያችሁ አለሁ።

ገጣሚ ምስራቅ ተረፈ አዲሱን የህብረተሰብ አመለካከት ጠንካራ መሰረት እንዲኖረው አድርጋ የቀየሰቻቸው የስነ ግጥም ምህንድስናዋን አለማድነቅ ንፉግነት ስለሚሆንብኝ ትንሽ ማለት ወደድኩኝ:: ምስራቅ ተረፈ ከአለባበሷ ጀምሮ አፃፃፏም አቀራረቧም ባሕላዊ ኢትዮጵያዊ ጨዋነትን የጠበቁ የሞራል ጭብጦችን ተጠቅማ በመሆኑ ለኔ ቢጤ የስነ ግጥም አድናቂዎች የነፍስ ምግቦች ነበሩ:: በእርግጥ በተለምዶ የውበት ተፈጥሮን የሚያሳዩ ብዙ የዕለት ተዕለት ገጠመኞችና ምሳሌዎች ቢኖሩም የምስራቅ ተረፈ ግጥሞች ግን የውበትን ዳኝነት ለመስጠትና የጥብብን ሚስጥር ለመረዳት እንደ መነሻ ጣዕም፣ ምናብ እና የተፈጥሮ ውበት ርዕሶች ሆነው አግኝቻቸዋለሁ::

ግጥሞቿ በሕይወታችን ውስጥ ትልቅ ሚና ስለሚኖራቸው የወደፊት ትውልዶች በሥነ ምግባር እንዲቀረፁ ይረዳሉ:: ገጣሚዋ ሕይወትን ከፍቅር ጋር አቆራኝታ በተለያየ እይታ፣ በተለየ መንገድ፣ ከተራ ነገር በላይ ለማየት፣ እንድንችል የሰላ ስሜቷን ገልፃበታለች::. ልክ እንደ አንድ ሰው ብዙ ትናንሽ ደም መላሽ ቧንቧዎች፣ የደም ስሮች፣ የአካል ክፍሎች እንዳሉት ሁሉ ምስራቅ ተረፈም ስነ ግጥሟን በዚህ ምሳሌ አሳይታበታለች።

በቀላል አገላለጽ ሥነ ግጥም አንድ ሰው የሚያምር ነገርን ወደ እውነት ለመተርጎምና ከእንደዚህ ዓይነቶቹ ነገሮች የውበት ደስታን ማግኘት እንደሚችል ማረጋገጥ ስለሆነ፣ ምስራቅ ተረፈ ይህንን ድርጊት በችሎታዋ ስትገልፀው በዓይናችን አይተናል:: ምስራቅ በደራሲ እና በአድማጭ መካከል የማይሰሙ የሚመስሉ የንግግር ክፍተቶችን ሞልታ በስነ ውብት ድር አስተሳስራ ሕይወት በመስጠት ሰሚ/አንባቢ/ተመልካች ዳግም አንድ አይነት ሊሆኑ እንዲችሉ፤ ሀ... ግእዝ፣ ሁ...ካዕብ ...ላ...ራብእ... እያለች የስነ ግጥምን ሀሁ አስቆጥራን አምሽታለች:: የጥበብ ባህሪው ደግሞ እውነታውን መወከል በመሆኑ የማቱ ሰላምን ዕድሜ ተመኘሁላት:: ለዛሬው በዚሁ አበቃሁ:: አብራችሁኝ፣ ስለ ቆያችሁ አመስግኜ መልካሙን ሁሉ ተመኘሁላችሁ። ሰላም!

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ተጠየቅ

# የፈጠራ ባስመብትነት ያስነሳው ውዝግብ

ሙሉቀን ታደገ

የዛሬው የፍረዱኝ አምድ ዝግጅታችን በመዲናችን አዲስ አበባ ከተማ የተፈጠረ ውዝግብን የሚዳስስ ነው። በደል ተፈጽሞብኛል ሲሉ ለአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል አቤት ያሉት ግለሰብ አትሌት ሙሉየ እያዩ ይባላሉ። አቤቱታ አቅራቢው ለዝግጅት ክፍላችን ቅሬታቸውን እንዲያመለክቱ የዳረጋቸው ፍሬ ነገር ከፈጠራ ባለንብረት ጋር የተያያዘ ነው።

አቶ ሰለሞን ገለታው የተባሉ ግለሰብ የአእምሮ ፈጠራዬ የሆነውን እና በኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን ተመዝግቦ እውቅና ተሰጥቶት ስሰራበት የቆየሁበትን የፈጠራ ስራ የራሳቸው ፈጠራ በማስመሰል ከኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን ፈቃድ በማውጣት የፈጠራ ስራየን ከህግ አግባብ ውጭ እየተጠቀመበት ይገኛል ሲሉ የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል አቤት ብለዋል። የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍልም ከሰዎች እና ከሰነዶች ያገኛቸውን መረጃዎች ዋቢ በማድረግ የኢትዮጵያ ህዝብ ግራ እና ቀኙን በማየት መፍረድ ይችል ዘንድ ዝግጅት ክፍሉ የደረሰበትን ሙሉ የምርመራ ውጤቱን እነሆ ብሏል። መልካም ንባብ።


### አትሌት ሙሉየ እያዩ ማን ናቸው ?

ከአቤቱታ አቅራቢው አትሌት ሙሉየ እያዩ ይባላሉ። በሩጫው ዘርፍ አሰልጣኝ እና አትሌት ናቸው። ከዚህም ባሻገር የብዙ ፈጠራዎች ባለቤት መሆናቸውን ከሰነዶች ተመለከትናል። ኢንተርናሽናል ክላይሜት ቼንጅ ኤንድ ስፖርት) ኢ.ተ.ሃ (Intrnational Claimate Change and Sport ኢ.ተ.ሃ) የተባለ ሃገር በቀል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት መስራች እና ስራ አስኪያጅ ናቸው። ድርጅቱ 306 አይነት የተለያዩ የስራ ዘርፎችን ይሰራል። የተለያዩ አለም አቀፍ የሽልማት ፕሮግራሞችንም ያዘጋጃል። ድርጅቱ በስፋት ሽልማት በማዘጋጀት ለተለያዩ አካላት ሽልማት ካበረከተባቸው ዘርፎች መካከል ስፖርት ፎር ክላይሜት ቼንጅ (Sport for Claimate Change) አንዱ ነው።

እንደ አትሌት ሙሉየ ገለጻ፤ ስፖርት ፎር ክላይሜት ቼንጅ (Sport for Claimate Change) ተብሎ የሚጠራው ዘርፍ በጣም ሰፊ አንድምታ አለው። ስፖርትን ከአየር ንብረት ጋር በማያያዝ ለመጀመሪያ ጊዜ በአለም አቀፍ ደረጃ ሽልማት ያዘጋጀው ኢንተርናሽናል ክላይሜት ቼንጅ ኤንድ ስፖርት) ኢ.ተ.ሃ (Intrnational Claimate Change and Sport ኢ.ተ.ሃ) የተባለ ሃገር በቀል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ነው።

ለአለም የአየር ንብረት ለውጥ የሁሉም አለም አገራት እጅ አለበት። ይህም በአለም ላይ የሚገኙ ስፖርተኞችን ስርዓተ ትንፈሳ በከፍተኛ ሁኔታ ሲጎዳ እየተስተዋለ ነው። ይሁን እንጂ አንድም አገር ሆነ ድርጅት ለአለም የአየር ንብረት መዛባት የራሴ ድርሻ አለበት ብሎ ሃላፊነቱን የሚወስድ ለአልነበረም። በዚህ ምክንያት ችግሩን በሚችሉት ደረጃ ለመቅረፍ ለረጅም ጊዜ በግላቸው ሲሰሩ ከቆዩ በኋላ ጉዳዩን የቅጅ እና ተዛማጅ መብቶች የህግ ከለላ ያስፈልገዋል ብለው በማመን ወደ ኢትዮጵያ አእምሯዊ ጥበቃ ባለስልጣን በመውሰድ እንዳስመዘገቡት ይናገራሉ። የኢትዮጵያ አእምሯዊ ጥበቃ ባለስልጣንም ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ በሰኔ 24 ቀን 2011 ዓ.ም የቅጅ እና ተዛማጅ መብቶች ምዝገባ ሰርተፍኬት እንደሰጣቸው ሰነዶች ያሳያሉ። ያገኙት ፈቃድም የአለም የአየር ንብረት ለውጥ በስፖርቱ ላይ ምን ያህል ተጽዕኖ እያሳዳረ እንደሚገኝ በአለም አቀፍ ደረጃ የአለምን ህዝብ በማነሳሳት ግንዛቤን ለመፍጠር የሚያስችል ነው።

ስፖርት እንቅስቃሴ ነው። ክላይሜት ቼንጅ ደግሞ የስርዓተ ትንፈሳ ሊያፋልስ የሚችል ነገር ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ ኢንተርናሽናል ክላይሜት ቼንጅ ኤንድ ስፖርት) ኢ.ተ.ሃ (Intrnational Claimate Change and Sport ኢ.ተ.ሃ) የተባለው አገር በቀል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ከዚህ ቀደም 115



የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን
Ethiopian Intellectual Property Authority

የቅጅና ተዛማጅ መብቶች የሚያስገኙ ስራዎች ምዝገባ የምስክር ወረቀት
Copyright & Neighboring Rights Registration Certificate

የማመልከቻ ቁ.:-5093/2014
Application No.

1. የመብት ባለቤት / Right owner's
1.1. ስም / Name:- ሙሉዬ እያዩ የሁሉጌታ
1.2. ጾታ / ወንድ Sex:- ዜግነት/ Nationality:- ኢትዮጵያዊ
1.3. አድራሻ /Address
ሐገር / Country:- ኢትዮጵያ ክልል/Regional State:- አዲስ አበባ
ክ/ከተማ/Sub-city/ የካ ዞን/Zone/:-
ወረዳ /Woreda/:- 02 ቀበሌ/Kebele:- የቤ ቁ./ House No:- 099
ስልክ ቁጥር / Tel. No.:- 09 44 34 23 03 ፖ.ሳ.ቁ/ P.O.Box:-
2. የፈጠራ ሥራው / Creative Work.
2.1. ርዕስ/Title:- አለም አቀፍ አደዋ ሽልማት
2.2. ምድብ/ Type :-ስነ-ጥበብ ንዑስ ምድብ /Sub-type:- ቅርፃ-ቅርፅ
2.3. የምዝገባ ቀን / Registration Date:- 13/04/2014 ዓ.ም
2.4. የምዝገባ ቁጥር / Registration No:- 3/3/015
2.5. የምስክር ወረቀቱ ህጋዊነት የሚያበቃበት ቀን/ Certificate's Date of Expiry:- 12/04/2019 ዓ.ም
3. የመብት ወሰን / Scope of right
Under the Proclamation of No 410/2004 Copyright and neighboring right Owner of copyright

ምዝገባውን ያፀደቀው ኃላፊ / Signed By:-
ወሰን ሙሉ
የቅጅ መብት ጥበቃና ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተወካይ
ቀን/ Date:- 13/04/2014 ዓ.ም



ማሳሰቢያ:-* ይህ የቅጅና ተዛማጅ መብት የሚያስገኝ ስራ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ቀዳሚ የባለቤትነት ማስረጃ በመሆን ያገለግላል::
* ይህ የምስክር ወረቀት በየአምስት ዓመቱ መታደስ አለበት::
Note:- * This copyright & neighboring right registration certificate serves as prima facie document of right ownership.
* This certificate has to be renewed every five years.

ሃገራት ሯጮች በኤንባሲዎቻቸው በኩል በመጥራት እና በኢትዮጵያ የሚገኙ የሁሉምን ክልሎች ሯጮች በማሳተፍ የ15 ኪሎ ሜትር የጎዳና ላይ ውድድሮችን በማድረግ ለአሸናፊዎች ሽልማቶችን አበርክቷል። በዚህም የአለም አቀፉ ማህበረሰብ የአየር ንብረት ለውጥ የስፖርቱን ዘርፍ ምን ያህል ተጽዕኖ እያደረበት እንዳለ ለማስገንዘብ መቻሉን ይገልጻሉ።

አቤቱታ አቅራቢው ከውድድር ባለፈም የስፖርት ፎር ክላይሜት ቼንጅ ጽንሰ ሃሳብን በተለያዩ አለማት እየተዘዋወረ ማስተማሩን ይናገራሉ። ለአብነት ያህል በብራዚል፣ በእንግሊዝ፣ ቻይና፣ ቤልጂም እና መሰል አገራት ላይ በአካል መጎብኘት የአየር ንብረት ለውጥ በስፖርቱ ላይ እያደረሰ ያለውን ተጽዕኖ ማስገንዘብ ችለዋል።

ሌላው ኢንተርናሽናል ክላይሜት ቼንጅ ኤንድ ስፖርት) ኢ.ተ.ሃ (Intrnational Claimate Change and Sport ኢ.ተ.ሃ) የተባለ አገር በቀል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ስር አለም አቀፍ ሽልማቶችን ከተደረገባቸው ዘርፎች መካከል በዛሬው ዝግጅታችን የምንመለከተው እና ለውዝግቡ መነሻ የሆነው አለም አቀፍ የአድዋ ሽልማት ተጠቃሽ ነው። አለም አቀፍ አድዋ ሽልማት በዋናነት የሚያተኩረው ከአገራችን ህልውና ጋር ተያይዞ ከፍተኛ መስዋእትነትን ለከፈሉ እና አገራችንን በአለም አቀፍ አደባባይ ስሟ በመልካም ነገር እንዲጠራ አስተዋጾ ለአበረከቱ ሰዎች ነው።

አለም አቀፍ የአደዋ ሽልማት የተሰኘው የፈጠራ ውጤት በአገራችን በአይነቱ የመጀመሪያ ነው። ይህን ፕሮግራም በኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን ራሱን ችሎ ተመዝግቦ ስራ ከመጀመሩ በፊት ኢንተርናሽናል ክላይሜት ቼንጅ ኤንድ ስፖርት) ኢ.ተ.ሃ (Intrnational Claimate Change and Sport ኢ.ተ.ሃ) በተሰኘ በኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን በተመዘገበ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ኤጀንሲ ስር ተመዝግቦ ከአደዋ ጋር ተያይዞ ሽልማት ለሚገባቸው ግለሰቦች ሽልማቶች ሰጥቷል።

አለም አቀፍ የአደዋ ሽልማት የሚዘጋጀው በአለም ዙሪያ ስለፍቅር፣ ለሰላም እና ለአንድነት ሲባል እውቀታቸውን፣ ሃብታቸውን እና ስልጣናቸውን በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ሆነው ለህዝባቸው እና ለአገራቸው እንዲሁም ለአለም ያበረከቱት አከላትን እውቅና ለመስጠት እና ሌሎች ሰዎችም ይህን መልካም ተሞክሮ ተመልክተው ለአገራችን ብሎም ለአለም አቀፉ ማህበረሰብ በጎ ስራዎችን እንዲሰሩ ለማድረግ ታስቦ ነው።

### የውዝግቡ መነሻ የሆነው አለም አቀፍ የአደዋ ሽልማት

የአለም አቀፍ የአደዋ ሽልማት ለመሸለም የፈጠራ ባለመብትነታቸው እንዲረጋገጥ እና የኢትዮጵያ የአእምሯዊ ንብረት ጥበቃ ባለስልጣንን ለበርካታ አመታት መጠየቃቸውን አቤቱታ አቅራቢው ይናጋራሉ። ይሁን እንጂ አለም አቀፍ የአድዋ ሽልማት ፕሮግራምን ለብቻው ነጥሎ መስራት እንደማይቻል እና አደዋ በራሱ የተለየ እና የህዝብ ንብረት የሆነን ነገር ለግለሰብ አይሰጥም ተባለ። በአገሪቱ ያሉ የማህበራዊ ማቋቋሚያ ህጎች አሳሪ ስለነበሩ እንደዚህ አይነት ነገሮችን ለግለሰቦች መስጠትን ስለሚከለክል ፈቃድ አንሰጥም መባላቸውን አቤቱታ አቅራቢው ይናገራሉ። ይህን ተከትሎ ፈቃድ ማግኘት ካልቻልኩ የአለም አቀፍ የአደዋ ሽልማትን ለማከናወን ምንድን ባደርግ ይሻላል? ሲሉ የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣንን እንደጠየቁ ይናገራሉ። ይህን ተከትሎ የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣንም ይህንን ሽልማት ማካሄድ ወይም ማከናወን በሚያስችል ተቋም ስር እንዲገቡ እና በዚያ ተቋም ስርም ሽልማት ፈቃዱን ማግኘት እንደሚችሉ ጠቁሟቸዋል።

ይህን በእንዲህ እንዳለ ስለጉዳዩ የፍትህ ሚኒስቴርን ለመጠየቅ እንደሄዱ እና በፍትህ ሚኒስቴርም ምንም ምላሽ የሚሰጣቸው አካል እንዳላገኙ አቤቱታ አቅራቢው ይናገራሉ። ለውጡን ተከትሎ አሳሪ የነበሩ ህግጋት ተነስተው ማህበራት ማደራጃ ወደ ሲቪክ ማህበረሰብ መጡ። በዚህም የአለም አቀፍ የአደዋ ሽልማት ፕሮግራምን በኢንተርናሽናል ክላይሜት ቼንጅ ኤንድ ስፖርት) ኢ.ተ.ሃ (Intrnational Claimate Change and Sport ኢ.ተ.ሃ) በተባለው አገር በቀል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ስር አስገብተነው እንደ አንድ የስራ ዘርፍ በማድረግ በ2011 ዓ.ም መመስረቱን ይናገራሉ።

ይህን ተከለትሎ አለም አቀፍ የአደዋ ሽልማት ፕሮግራምን ከመጋቢት 15 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ስራውን አስጀመረ። ከመጋቢት 15 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ እስካሁንም ድርጅቱ ትልልቅ ስራዎችን እየሰራ መቆየቱን አቤቱታ አቅራቢው ይናገራሉ። በተለይም 125ኛው የአድዋ ድል በዓል ሲከበር የካቲት 23 ቀን 2013 ዓ.ም በአለም አቀፍ ደረጃ በአለም ዙሪያ ስለፍቅር፣ ለሰላም እና ለአንድነት ሲባል እውቀታቸውን፣ ሃብታቸውን እና ስልጣናቸውን በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ሆነው ለህዝባቸው እና ለአገራቸው እንዲሁም ለአለም ያበረከቱት አካላትን ማወዳደራቸውን እና ለመጀመሪያ ጊዜም የአለም አቀፍ የአደዋ ሽልማት የተሰጠውም ለእቴጌ ጣይቱ እና ዳግማዊ አጼ ምኒሊክ መሆኑነን ይናገራሉ። ምክንያቱም ለአድዋ ድል ፋና ወጊ የነበሩት እቴጌ ጣይቱን እና ዳግማዊ አጼ ምኒሊክ ስለመሆናቸው አቤቱታ አቅራቢው ያብራራሉ።

እቴጌ ጣይቱን እና ዳግማዊ አጼ ሚኒሊክ በህይወት የሉም። በህይወት ባይኖሩም ለእነሱ ሽልመናል። አጼ ምኒሊክ እና እቴጌ ጣይቱ በህይወት ስለሌሉ ባለፉት ዘመናት በጀግንነት ለአገራቸው ዋጋ በመክፈል ገድል የሰሩ አባት አርበኞች እና እነሱን ይወክላሉ ብለው ለአሰቧቸው የጎንደር አባት አርበኞች ሽልማቱን ማበርከታቸውን ያስረዳሉ። ሽልማቱም ስነ ሥርዓት ከጎንደር ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር የተደረገ እንደነበር ጠቁመዋል።

መጋቢት 15 ቀን በ2012 ዓ.ም ድርጅቱ በይፋ አለም አቀፍ የአደዋ ድል ሽልማት ፕሮግራም እንጀመረ እና ከዚህ ጀምሮ ድርጅታቸው አለም አቀፍ የአደዋ ድል ሽልማት ፕሮግራም እንደሚያስቀጥለው በጋዜጣዊ መግለጫ ለመገናኛ ብዙሃን ማሳወቃቸውን ይናገራሉ። በ2013 ዓ.ም የኮቪድ ወቅት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ አገራችን ብሎም አለማችን በበርካታ ውስብብስብ ችግሮች ውስጥ እየተፈተኑ ቢሆንም እንኳን ድርጅቱ የሽልማት ስራውን እንዳላቋረጠ አቤቱታ አቅራቢው ተናግረዋል።

በኢንተርናሽናል ክላይሜት ቼንጅ ኤንድ ስፖርት) ኢ.ተ.ሃ (Intrnational Claimate Change and Sport ኢ.ተ.ሃ) በተባለው አገር በቀል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ሽልማት ከሰጠን ከሁለት ወር በኋላ አቶ ሰለሞን ገለታው የተባሉ ሌላ ግለሰብ አደዋ አዋርድ በዩቲውብ ብለው ሽልማት ሰጡ። የምዝገባ ስሙም አደዋ ሽልማት በዩቲውብ ብሎ ነው የተመዘገበው። ሙሉ አሰራሩን ግን ኢንተርናሽናል ክላይሜት ቼንጅ ኤንድ ስፖርት) ኢ.ተ.ሃ (Intrnational Claimate Change and Sport ኢ.ተ.ሃ) ከተባለው አገር በቀል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ሙሉ በሙሉ ተመሳሳይነት ያለው ነው።

አቶ ሰለሞን ገለታው በኢንተርናሽናል ክላይሜት ቼንጅ ኤንድ ስፖርት) ኢ.ተ.ሃ (Intrnational Claimate Change and Sport ኢ.ተ.ሃ) የተባለውን አገር በቀል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት አሰራር በሙሉ ማግኘት የቻሉበት በርካታ ምክንያቶች አሉ። ከእነኝህ ምክንያቶች አንዱ በመጋቢት ወር በ2011 ዓ.ም ከሽልማቱ ጋር ተያይዞ የጋዜጣዊ መግለጫ እንደሰጡ እና በዚያ ጋዜጣዊ መግለጫም አቶ ሰለሞን ገለታው መገኘታቸው ሲሆን፤ በ2013 ዓ.ም 125ኛው የአደዋ ድል በዓል ሲከበር የነበረው ሙሉ ሂደት ደግሞ በመገናኛ ብዙሃን ተላልፎ ስለነበር መረጃውን ከመገናኛ ብዙሃን አግኝቷል። ከመገናኛ ብዙሃን ባለፈ ስለ ሽልማቱ በማህበራዊ ድህረ ገፅ ላይ በስፋት

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ተጠየቅ

ሃሳቡ ተንሸራሸሯል። አቶ ሰለሞንም ሃሳቡን ከዚህ በመውሰድ አደዋ አዋርድ በዩቲዩብ ብሎ እንደመሰረተ እርግጠኛ መሆናቸውን ይናጋራሉ።

እንደ አቤቱታ አቅራቢው ገላጻ፤ ከ2013 ዓ.ም በፊት ባሉ ጊዜያት የአለም አቀፍ አደዋ ሽልማትን ብቻውን ከኢንተርናሽናል ክላይሜት ቼንጅ ኤንድ ስፖርት) ኢ.ተ.ሃ (Intrnational Claimate Change and Sport ኢ.ተ.ሃ) ከተባለው አገር በቀል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ውጪ ይሰጠን ብለው ጠይቀው ነበር። ነገር ግን የኢትዮጵያ አእምሯዊ ጥበቃ ባለስልጣን ፈቃድ አልሰጥም በማለት ከልክሎ ነበር። ለዚህም እንደምክንያ የተጠቀሰው አድዋ የህዝብ ነው የሚል ነበር።

ነገር ግን አቤቱታ አቅራቢው ስንት አመት ጠይቀው ያልተፈቀደላቸውን የስራ የአቤቱታ አቅራቢውን የስራ ፈጠራን ለሰረቀው ሰው የአደዋ አዋርድ ሽልማትን መስጠት እንደሚቻል እና ፈጠራውም የአቶ ሰለሞን ገለታው አድርጎ በመቁጠር ፈቃድ እንደተሰጠው አቤቱታ አቅራቢው ይናገራሉ። ይህን ተከትሎ እንዴት የአእምሮ ባለንብረትነት ጥበቃ ባለስልጣን የአንድ ድርጅት ሆኖ ሳለ፤ ከዚህ ቀደም ሽልማቱ ኢንተርናሽናል ክላይሜት ቼንጅ ኤንድ ስፖርት) ኢ.ተ.ሃ (Intrnational Claimate Change and Sport ኢ.ተ.ሃ) በተባለው አገር በቀል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ስር እየተሰራበት እያለ ለሌላ ሰው እንዴት ፈቃዱ ለሌላ ሰው ይጣል ? ሲሉ የኢትዮጵያን አእምሯዊ ንብረት ጥበቃ ባለስልጣንን መጠየቃቸውን ይገልጻሉ።

የኢትዮጵያን አእምሯዊ ንበረት ጥበቃ ባለስልጣንን ለዘመናት ምክንያት እየፈጠረ ሽልማቱን ረሱን ችሎ እንዳይሄድ ሲከለክል እንዳልነበር ሁሉ ለአቶ ሰለሞን ፈቃድ ከሰጠ በኋላ አንተም ለመሸለም ፈቃድ መውሰድ ትችላለህ ብሎ እንደመለሰላቸው እና ባለስልጣን መስሪያቤቱ እርሳቸውን የአለም አቀፍ የአደዋ ሽልማት መሸለም አንዲችሉ ፈቃድ አንደሰጣቸው ይናገራሉ። ከዚህ በተጨማሪም ባልስጣን መስሪያ ቤቱ አቶ ሰለሞን ያመጣውን ፈጠራ የመዘገብነው የሽልማት ዋንጫውን ምስል እንጂ ሽልማት እንዲሰጥ አይደለም። ሽልማት እየሰጠ ከሆነ ለዚህ ስራው ቢከሰስም ቢታሰርም ራሱ ኃላፊነቱን የሚወስድ ይሆናል የሚል ምልሽ እንደሰጧቸው ይናገራሉ።

### ከሰነዶች የተገኙ ማስረጃዎች

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ለጎንደር ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽህፈት ቤት በቁጥር ባ/ቱ/ስ/መ/9594116-1/2013 በቀን 07/01/2013 እንደተመለከተው ኢንተርናሽናል ክላይሜት ቼንጅ ኤንድ ስፖርት) ኢ.ተ.ሃ (Intrnational Claimate Change and Sport ኢ.ተ.ሃ) የተባለው አገር በቀል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት በውስጡ ከያዛቸው 306 በላይ የመፍትኄ ኃሳብ ስራዎች መካከል ለሰዎች ስለ ሰላም፣ ፍቅር፣ ተስፋ ሲባል ኃብታውቸውን፣ እውቀታቸውን እና ስልጣናቸውን በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ሆነው ለህዝባቸው፣ ለህገራቸው፣ ለዓለም ማህበረሰብ እና ለማንኛውም ችግር በመፍትሄነት ጥሩ ስራ ለሰሩ ሰዎች የሚሸልሙበት አለም አቀፍ የአደዋ ሽልማት ፕሮግራም በጎንደር ከተማ በ2013 ዓ.ም እንዲካሄድ ስለጠየቁ፤ የጠየቁት ጥያቄ የታለመለትን ግብ እንዲመታ የከተማ አስተዳደሩ ትብብር ይደረግላቸው የሚል ነው ።

ይህን ተከትሎ የጎንደር ከተማ ከንቲባ ጽህፈት ቤት በቁጥር የጎ/ከ/አስ/ከ/2219/ሥ/220 በቀን 19/04 /2013 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ እንዳመላከተው ኢንተርናሽናል ክላይሜት ቼንጅ ኤንድ ስፖርት) ኢ.ተ.ሃ (Intrnational Claimate Change and Sport ኢ.ተ.ሃ) የተባለው አገር በቀል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት በየካቲት 23/2013 ዓ.ም በጎንደር ከተማ ሽልማት ማካሄድ እንደሚችሉ ያስረዳል። እዚህ ላይ ከሰነዶች እንደምንረዳው አቤቱታ አቅራቢው አለም አቀፍ የአደዋ ሽልማትን ይሰጡ እንደነበር ነው።

### መመሪያዎች ምን ይላሉ?

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 91(3) ላይ መንግሥት አቅም በፈቀደ መጠን ኪነ ጥበብን፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂን የማስፋፋት ግዴታ እንዳለበት



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
AGENCY FOR CIVIL SOCIETY ORGANIZATIONS

የምዝገባ የምስክር ወረቀት

ኢንተርናሽናል ክላይሜት ቼንጅ ኤንድ ስፖርት ኢ.ተ.ሃ የተባለ አገር በቀል ድርጅት በአዋጅ ቁጥር 1113/2011 መሠረት ሰኔ 24 ቀን 2011 ዓ.ም. በመዝገብ ቁጥር 4244 በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ ተመዝግቦ ሕጋዊ ሰውነት ተሰጥቶታል።

CERTIFICATE OF REGISTRATION

This is to certify that INTERNATIONAL CLIMATE CHANGE AND SPORT ኢ.ተ.ሃ has been registered and accorded legal personality with Registry Number 4244 on July 1, 2019 as Local Organization in accordance with the Civil Society Organizations Proclamation No. 1113/2019.

ጂማ ዲልቦ ደንበል
ዋና ዳይሬክተር
Jima Dilbo Denbel
Director General

Notice If the organization fails to discharge its responsibility to submit Activity and Audit reports as per Proclamation No 1113/2019 Article 70 of the proclamation "verification of existence" shall be applicable

For more information
Tel +251115582422
P.O.Box 14340
E-mail: info@chsa.gov.et
Website www.chsa.gov.et

ይደነግጋል። በዚሁ መሠረት መንግሥትም የቅጅና ተዛማጅ መብቶችን ለማክበርና ለማስከበር ይረዳው ዘንድ አዋጅ ቁጥር 410/1996 በማውጣት ሥራ ላይ አውሎ በመተግበር ላይ ይገኛል። የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ሁል ጊዜ እያደጉ እና እየተለዋወጡ የሚሄዱ በመሆናቸው በአዋጅ ቁጥር 410/1996 ላይ የተወሰነ ማሻሻያና ጭማሪ በማስፈለጉ ይህ አዋጅ በአዋጅ ቁጥር 872/2007 ማሻሻያ አድርጎ በሥራ ላይ አውሏል። ይህም መሆኑ ከአለም እና ከተለዋዋጭ ሁኔታዎች ጋር ለመራመድ ያስችላል።

ከአገራችን ነባራዊ ሁኔታ በመነሳት የቅጅና ተዛማጅ መብት ጽንሰ ሀሳብ እንደሚከተለው ያብራራል። የቅጅ መብት ማለት የኪነ-ጥበብ፣ ዕደ-ጥበብ፣ የሥነ-ጽሑፍና የሳይንስ መስክ የፈጠራ ሥራዎች ባለቤቶች በፈጠራ ሥራዎቻቸው ላይ የሚኖራቸው የአእምሯዊ ንብረት መብት ነው። ይህ መብት የኢኮኖሚና የሞራል መብቶችን የሚያካትት ነው። የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ ዓላማ የፈጠራ ባለሞያዎች የፈጠራ ሥራዎቻቸውን ለማከናወን ያፈሰሱትን እውቀት፣ ጊዜና ኃብት እንዲያካክሱና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚ ሆነው ለተጨማሪ የፈጠራ ሥራ እንዲነሳሱ ለማድረግ ነው። በመሆኑም የቅጅና ተዛማጅ መብቶች መጠበቅ ቀጣይ የፈጠራ ሥራን ለማበረታታትና ኢንቨስትመንት እንዲበረታታ አቅም ለመፍጠር የሚያግዝ ነው።

በጥቅሉ ኮፒራይት የፈጠራ ባለመብቶችን የሞራል መብት በማስጠበቅና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚ በማድረግ ቀጣይነት ያለው የፈጠራ ሥርዓት ለመፍጠር የሚያስችል እና በህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሳይንሳዊና ቴክኖሎጂያዊ እድገት በህብረተሰቡ ውስጥ እንዲያመጡ ማድረግ ነው።

በአሁኑ ሰዓት የቅጅና ተዛማጅ መብቶችን በተመለከተ ጥበቃ የሚያደርግላቸው በ1996 ዓ.ም የወጣው አዋጅ ቁጥር 410/1996 እና ይህንን አዋጅ ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 872/2007 ናቸው። አዋጅ ቁጥር 872/2007 በአዋጅ ቁጥር 410/1996 ውስጥ የተካተቱ የተወሰኑ አንቀፆች ላይ ማሻሻያ ያደረገ እና አዲስ መብቶችን ያካተተ ነው። በመሆኑም አዲሱ አዋጅ ነባሩን አዋጅ ቁጥር 410/1996 ሙሉ ለሙሉ የሻረ አይደለም።

በአዋጅ ቁጥር 410/1996 አንቀጽ 2(8) ላይ "የቅጅ መብት ማለት ከአንድ ሥራ የሚመነጭ የኢኮኖሚ መብት ሲሆን አግባብነት ባለው ጊዜ የሞራል መብቶችን ይጨምራል" በማለት ትርጉም ይሰጠዋል። ከትርጉሙ እንደምንረዳው የቅጅ መብት የሥራው አመንጪ የሆነው ሰው ከሥራው የሚያገኘው ኢኮኖሚያዊ እና የሞራል መብት ነው። እነኚህ የሥራው አመንጪ መብቶች በአንቀጽ 7 እና 8 ላይ ተገልፆ ይገኛሉ። የሥራው አመንጪ የራሱን አእምሮ ውጤት የሆነውን የፈጠራ ሥራ ማለት የሥነ ጽሑፍ፣ የኪነ ጥበብ፣ ዕደ-ጥበብ እና የሳይንሳዊ መስኮች በተለይም መጽሐፍ፣ ቡክሌት፣ በመጽሔት ወይም በጋዜጣ ላይ የሚገኝ መጣጥፍ፣ የኮምፒዩተር ፕሮግራም፣ ንግግር፣ ሌክቸር፣ የሀይማኖት ስብከት፣ ድራማ፣ ድራማዊ ሙዚቃ ሥራ፣ የመድረክ ውዝዋዜ፣ የኦዲዮ ቪዥዋል ሥራ፣ የኪነ ህንፃ ሥራ፣ የስዕል የቅብ፣ የቅርፃ ቅርጽ ሥራ፣ የፎቶ ግራፍ ሥራ፣ ስዕላዊ መግለጫ፣ ካርታ ፕላን እና የመሳሰሉት ሥራዎች ላይ ኢኮኖሚያዊ እና የሞራል መብትን ያገኛል።

በአዋጁ አንቀጽ 2 (14) ላይ "ተዛማጅ መብት ማለት ከዋኝ፣ የድምጽ ሪከርዲንግ ፕሮዲውሰር፣ የብሮድካስቲንግ ድርጅት በሥራው ላይ ያለው መብት ነው" በማለት ትርጉም ሰጥቶታል። የተዛማጅ መብቶች ባለቤት በሥራው ላይ የሁለተኛ ደረጃ መብት ነው ያላቸው። በሥራው ላይ የመጀመሪያ ደረጃ መብት ያለው የሥራው አመንጪው ነው።

የፈጠራ ባለቤትነት መብትን ለማስጠበቅ አዋጁ የራሱ የሆ የተፈጻሚነት ወሰን፣ ጥበቃ ለማግኘት የሚስፈልጉ መመዘኛዎች እና የብቸኝነት ተፈፃሚነት ወሰን አስቀምጧል። በዚህ መሰረት ጥበቃ ለማግኘት የሚያስፈልጉ መመዘኛዎች] አንደኛው የሥነ-ጽሑፍ፣ ኪነ-ጥበብ ወይም በሳይንሳዊ መስክ ፈጠራ የሆነ ሥራ የሥራው አንጪው የአዕምሮ ውጤት እስከሆነ ድረስ የሥራው ዓላማና ጥራት ደረጃ ግምት ውስጥ ሳይገባ ወጥ (ኦርጅናል) ከሆነ እና የተቀረጸ ወይም ግዙፍነት ካገኘ ሥራው በመውጣቱ ብቻ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ጥበቃ እንዲያገኝ በአዋጅ ቁጥር 410/1996 አንቀጽ 6(1) ላይ ተገልፆል። በመሆኑም የሥራው አመንጪ ለሥራው ጥበቃ ለማግኘት ሥራው 1ኛ ወጥ (ኦርጅናል) መሆን ያለበት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሥራው ግዙፋዊነት ያገኘ መሆን እንዳለበት እንደ ቅድመ ሁኔታ ተቀምጧል።

ከዚህ በተጨማሪ አዋጁ ህግን ተላልፎ በተገኙ ግለሰቦች፣ ቡድኖች እና ድርጅቶች ላይ ምን አይነት እርምጃ ሊያስወስድ እንደሚችል በግልጽ ተመላክቷል። ከዚህ ጋር ተያይዞ የአእምሯዊ ንብረት ትሪቡናል/ የዳኝነት ሥልጣን የማን ነው የሚለውም በግልጽ ተቀምጧል። በዚህ መሰረት፡- በነባሩ አዋጅ ቁጥር 410/1996 ላይ እንደተመለከተው ማንኛውንም በቅጂና ተዛማጅ መብቶች ጥሰትን በተመለከተ የሚነሱ ፍትሐብሔራዊ ክርክሮችን የሚዳኘው መደበኛው ፍርድ ቤት እደሆነ በአንቀጽ 33 እና 34 ተደንግጎል።

በቅጂና ተዛማጅ መብቶች በባህሪያቸው ለየት ያለ የተወሰነ እውቀትን በጉዳዩ ዙሪያ የሚጠይቁ ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ የማስረጃዎቻቸው በባህሪያቸው ውስብስብ በመሆናቸው በመደበኛ ፍርድ ቤት ላይ ከመደበኛ ሥራቸው ላይ ጫና የሚያሳድሩ እና የጉዳዩ መጎተትን የሚያስከትሉ በመሆናቸው እና በተግባርም ይኸው እያጋጠመ ያለ ችግር ነው። በመሆኑም እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ሲባል በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 872/2007 ውስጥ መፍትሄ ማስቀመጥ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል። በዚሁ መሠረትም በተሻሻለው አዋጅ ውስጥ በቅጂና ተዛማጅ መብቶች የሚነሱ ከውል ውጭ ስለሚደርስ ሃላፊነት የሚመለከቱ ጉዳዮች በስተቀር የፍትሐብሔር ክርክሮችን የመዳኘት ስልጣን የሚኖረው በአእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በሚያቋቁመው የአእምሯዊ ትሪቡናል እንደሚሆን ደንግጎል።

ነገር ግን ይህ ትሪቡናል እስኪቋቋም ድረስ ክርክሩን የመዳኘት ስልጣኑ የመደበኛው ፍርድ ቤት ሆኖ እንደሚቀጥል ተጠቅሷል። ይህ ትሪቡናል ከተቋቋመ በኋላ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የሕግ ስህተት አለ የሚል ተከራካሪ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት በ60 ቀናት ውስጥ ይግባኙን ማቅረብ እንደሚችልም ተገልፆል።

በሁለቱ ግለሰቦች መካከል ስለተፈጠው ነገር ማብራሪያ እንዲሰጡን የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጥበቃ ባለስልጣን በደብዳቤ የጠየቅን ቢሆንም ከችግሩ ከብደት አንጻር ጉዳዩን በጥልቀት ማብራራት ስለሚጠይቅ ስለጉዳዩ በበቂ ደረጃ በማጣራት ትክክለኛውን መረጃ ባገኙ ጊዜ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደሚገልጹ ባለስልጣን መስሪያቤቱ ገልጾዋል። ከዚህም በተጨማሪ አቶ ሰለሞን ገለታውንም ለማግኘት ያደረግነው ሙከራ አልተሳካም። ስለዚህ ከዚህ ጋር በበተያያዘ ሃሳብ አለኝ የሚል ማንኛውም አካል ቢመጣ የምናስተናገድ መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# በዳዴ እሽቅድምድም

"ዳዴ"፡- ጨቅላ ሕጻናት ቆመው ለመሄድ የሚውተረተሩበት ተፈጥሯዊ የዕድሜያቸው ባህርይ ነው። "ወፌ ቆመች!" እየተባሉ ሲውተረተሩ ማየት እንኳን ለወላጆች ቀርቶ ለተመልካችም ቢሆን ደስታው እጥፍ ድርብ ነው። ሕጻናቱ አጥንታቸው ጠንክሮ ያለ ድጋፍ መቆም እስከሚችሉበት ጊዜ ድረስ ያለችው ያቺ አጭር ዕድሜ የምታሳሳና ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚደረግባት ወቅትም ነች። ሕጻናቱም ቢሆኑ ሲደነቃቀፉ ማልቀስ፣ መነጫነጭና እምባቸውን በማፍሰስ ስሜታቸውን መግለጽ የተለመደ ባህርያቸው ነው።

በግድ ካልቆምን ብለው ከተፈጥሯቸው ጋር ሲታገሉና ሲውተረተሩ መውደቃቸውና መላላጣቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በወላጆቻቸው "የእንትፋቱፍ ሸንገላ" የወደቁበት መሬትና ያደነቃቀፏቸው ቁሳቁስ በጥፊ እየተመቱላቸው ማባበልም የተለመደና ከጨቅላ ሕጻናቱ አስተዳደግ ጋር የተያያዘ ሌላው አዝናኝ ትርዒት ነው።

ማቲዎቹ በተሰበሰቡበት አንድ ክፍል ውስጥ መጫወቻ ከፊት ለፊታቸው በመወርወር እየዳኹም ሆነ ዳዴ እያሉ ተሽቀዳድመው እንዲያመጡ የሚደረገው ትእይንትም ብዙ የሚባልለት ነው። በዳዴ "ሩጫቸው" እየተውተረተሩ መጫወቻውን ቀድሞ ለመንጠቅ የሚያሳዩት ግብግብ ብቻ ሳይሆን "ለእኔ ብቻ ካልሆነ" በማለት የሚገጥሙት ትግል፣ ትርምስና የ"ተበለጥን" መጯጯኽም ሌላው የዘመናቸው መታወቂያ ነው። ልጅነት እንደሚባለው ጅልነት ሳይሆን "ማርና ወተት" እየተባለ የሚንቆለጳጰሰውም እነዚህን መሰል የጨቅላነት የዕድሜ ውበቶች እንደተወደዱ በተፈጥሮ "ቸርነት" ከትውልድ ትውልድ እየተላለፉ ስለሚኖሩ ጭምር ነው።

ይህን መሰሉ መልካም የጨቅላነት ዕድሜ ትሩፋት የሚወደደውና የሚናፈቀው ሁሌም በጊዜው ሲስተዋል ነው። በዕድሜያቸው ድኸውና ዳዴ ብለው ከማደግ ይልቅ መንፏቀቁንና ዳዴ ማለቱን የሙጥኝ የሚሉ ሕጻናት አንድም የጤና ችግር ወይንም የአስተዳደግ ጉድለት ያለባቸው ብቻ ናቸው። በጊዜው ያልዳኸ፣ በወቅቱ ዳዴ እያለ ያላደገና የማያድግ ሕጻን ለቤተሰብ የሀዘን ምክንያት፤ ለሆስፒታልም ቤትኛ ሆኖ ከመኖር ውጭ ሌላው አማራጭ የጠበበ ይሆናል። "ለሁሉም ጊዜ አለው" በማለት ጠቢቡ ሰሎሞን የተወልን ታላቅ ምክርም እዚህ ቦታ ቢጠቀስ መልካም ይሆናል።

### ከዳዴ እሽቅድምድም ያልተላቀቀው ፖለቲካችን፤

አብዛኞቹ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተወልደው የሚሞቱት ገና በዳዴ ዕድሜ ላይ እያሉ ነው። ረጅም ዕድሜ ይቆያሉ ቢባል እንኳን አኗኗራቸው ገና በጠዋቱ በመከፋፈል ልምሻ ስለሚለከፍ ነፍስ አውቆ ዓላማን ማስፈጸም ብርቅ እየሆነባቸው በአጭሩ የሚቀጩት ከእንፉቅቅ መዳኸ ሳይላቀቁ ነው። በኢትዮጵያ የፖለቲካ ዜና መዋዕል ውስጥ ለሥልጣን የሚደረገው የቡድኖች ትርምስ የቃላት ምርጫ ሳያስፈልግ ከጨቅላ ሕጻናት የመጫወቻ ቅሚያ ፍልሚያ ጋር የሚመሳሰል ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም።

ለምሳሌ፡- ፊውዳላዊው ሥርዓት ማኅበር በዴሞክራሲ ፈለግ እንዲመራ ለማድረግ የኢትዮጵያ ለውጥ አላሚ ወጣቶች የከፈሉት መስዋዕትነት ይህ ቀረሽ የሚባልለት አልነበረም። ብዙዎች ለዴሞክራሲ እውን መሆን ታግለዋል። የሕይወት መስዋዕትነት ለመክፈል እንኳን ሳይሳሱ "ጭዳ ሆነው" በነፍሳቸው በመወራረድ የማይተካ ደማቸውን ለዓላማቸው ገብረው አልፈዋል።

"መሬት ላራሹን!" እየፈከሩ፣ "ያልተማረ ይማር!" የሚል ምኞት እየዘመሩ፣ "ዲሞክራሲ በኢትዮጵያ ምድር እንዲሰፍን እየታገሉ"፣ "ሕዝባቸው ከድህነት እንዲላቀቅ" አምርረው ሥርዓቱን እየተቃወሙ የወደቁና እንደ ሻማ ቀልጠው ያለፉ የሕዝብ ልጆች ቁጥራቸው ሺህ ምንተሺ ነው። ዳሩ ምን ያደርጋል! ይህንን ለለውጥ የጨከነ ትውልድ የመሩትና ያስማሩት መሪዎቻቸው በሥልጣን ጥምና ርሃብ ናውዘው የሰከሩ ስለነበሩ "እኛ እያሉ ወጣቱን እያስፈከሩ፤ ለእኔነት የግል ጥቅማቸው" መቃዠትን ስለመረጡ ያ የለውጥ ኃይል እንዲበተንና ደሙ "ደመ ከልብ" ሆኖ እንዲቀር ፈርደውበታል።

ንጉሣዊ ሥርዓቱ ከመንበሩ እንዲወገድ ለጥቂት ዓመታትና ወራት ያህል ታግለው በማታገል የፊት አውራሪነቱን ሚና የተጫወቱትና በተለያየ ስም ይታወቁ የነበሩ ግራ ዘመም የህቡዕ ታጋዮችና የአደባባይ ተፋላሚ አመራሮች የሚመሩትን ኃይል በጥበብ፣ በማስተዋልና በውይይት አስተባብሮና መርቶ ወደ ጋራ ግባቸው ከማድረስ ይልቅ "የዳዴ እንፉቅቅን የሙጥኝ ብለው" እርስ በእርስ መቦጫጨቅና መገዳደልን ተቀዳሚ ምርጫ በማድረጋቸውም መንጋቸው ተበታትኖ፣ እነርሱም ነፋስ እንደገባው እብቅ የት ደረሱ ሳይባል በከንቱ ባክነው ቀርተዋል።

አንዳንድ ፀረ አገርና ሕዝብ ፓርቲ ተብዬዎችም ለሱማሊያው እብሪተኛ መሪ ለዚያድ ባሬ ወራሪ ሠራዊት "አለኝታ በመሆን" በታሪክ ይቅር የማይባል ክህደት መፈጸማቸው የሚዘነጋ አይደለም። ያ "የሻምላ ትውልድ" እርስ በእርስ መፋለሙ ብቻም ሳይሆን ትግሉን አኮላሽቶ ለወታደራዊው ደርግ አሳልፎ መስጠቱም ሌላው "የዳዴ እንፉቅቅ ዘመኑ" መገለጫ ነው።

በዘመነ ደርግ የመጀመሪያው ዓመታት ግድም በኢማሌድኅ (የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች ኅብረት) ጃንጥላ ሥር ለመሰባሰብ የሞከሩት "የዳዴ ተንፏቃቂ ስብስቦችም"፤ "የማይዘልቅ ማሕበር በጠጅ ይጀመራል" እንዲሉ፤ የጨቅላ ስብስባቸው የተጠናቀቀው መጠፋፋትን ምርጫ በማድረግ ነበር። በቀይና በነጭ ቀለማት የተወከሉት አገራዊ ሽብሮችም የምን ያህሉን ወጣቶችና ጎልማሶች ሕይወት እንደቀሰፉ በጥቁር ቱቢት የተሸፈኑትን የታሪክ ድርሳኖቻችንን ብንፈትሽ እውነቱን በግልጽ ይመሰክሩልናል።

የዘመነ ኢህአዴግ የፖለቲካ ፓርቲዎች የዳዴ እሽቅድምድምም ገና ከጅምሩ በልምሻ የተለከፈ ነበር። በረኸኞቹ "ጌቶች" በምድረ በዳ የቀመሩት "ጨቅላ የፖለቲካ ቡድኖችን አሽመድምዶ ማስገበር" ስትራቴጂ ተተግብሮ የተሳካላቸው መቶ በመቶ ነበር ማለት ይቻላል። ከጎጥና ከብሔር ጋር "ጡት በማጣባት" የፈለፈሏቸው ቡድኖች እንዴት እንደኖሩና እንደሞቱ፣ እንዴትም እየኖሩ እንዳሉ የምናውቀው ስለሆነ ሙት ወቃሽ ሆነን ዜና እረፍታቸውን "መቃብራቸው ላይ ቆመን" መተረኩ አስፈላጊ ላይሆን ይችላል። በእንፉቅቅ መኖሩ የተጣባቸው አንዳንድ "የልምሻው ዘመን ቅሪቶችም" የዕድሜ አዛውንት ፀጋቸውን አዋርደው የአስተሳሰብ ድንክዬ በመሆን እስካሁንም በጨቅላ ድርጊቶቻቸው ጤና እየነሱን እረፍት እንዲርቀን ምክንያት ሆነዋል።

የኢትዮጵያን ፖለቲከኞች የሚገልጽና ስሜትን ፈታ የሚያደርግ አንድ የግል ገጠመኝ ላስታውስ። ይህ ጸሐፊ በዘመነ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪነቱ የጄኔራል ዊንጌት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አንድ "ዝነኛ" የህንድ መምህር ስም ተደጋግሞ ሲነሳ ያደምጥ ነበር። የጸሐፊው መኖሪያ ከትምህርት ቤቱ ተጎራባች ስለነበር ከጓደኞቹ ሪፖርት ብቻ ሳይሆን በጉርብትናም ጭምር መምህሩን በሚገባ ያውቀዋል።

ይህንን መምህር "ዝነኛ" ያሰኘው የዕውቀት አቅሙና የማስተማር ችሎታው ሳይሆን ታሪኩ ሌላ ነው። መምህሩ ቢያንስ ከሠላሳ እስከ አርባ ዓመት ለሚገመት ጊዜ በማስተማር ላይ በቆየበት እዚያ ት/ቤት ውስጥ የሚያስተምረው ኢትዮጵያ ከመምጣቱ አስቀድሞ ባዘጋጀው የማስታወሻ ደብተር እንጂ በአዲስ አቀራረብና ዝግጅት ለተማሪዎቹ እንደ ወቅቱ ማሻሻያ እያደረገ አልነበረም። ያቺ ዕድሜ ጠገብ የማስታወሻ ደብተሩ ከማርጀቷና ከመተሻሸቷ የተነሳ መልኳ ራሱ ወይቦ ከእርሱ ውጭ ማስታወሻውን የሚያነብ ሌላ ሰው ስለመኖሩ እርግጠኛ መሆን አይቻልም ነበር።

> የዘመነ ኢህአዴግ የፖለቲካ ፓርቲዎች የዳዴ እሽቅድምድምም ገና ከጅምሩ በልምሻ የተለከፈ ነበር። በረኸኞቹ "ጌቶች" በምድረ በዳ የቀመሩት "ጨቅላ የፖለቲካ ቡድኖችን አሽመድምዶ ማስገበር" ስትራቴጂ ተተግብሮ የተሳካላቸው መቶ በመቶ ነበር ማለት ይቻላል

ከበርካታ ዐሥርት ዓመታት በኋላ ት/ቤቱ ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤትነት ወደ ኮንስትራክሽን ኮሌጅነት አድጎና ይህ ጸሐፊም ወግ ደርሶት በዚያ ት/ቤት በትርፍ ሰዓት መምህርነት ለማገልገል ዕድል ባገኘባቸው ዓመታትም ያ መምህር ይጠቀም የነበረው በዚያችው ማስታወሻ ደብተር ነበር። ብዙ ተማሪዎች የዚህን መምህር ባህርይና የማስተማሪያውን ደብተር ምሥጢር ስለሚያውቁ በእርሱ ክፍለ ጊዜ ከመግባት ይልቅ ከቀዳሚዎቹ ተማሪዎች ደብተር በመዋስ ማጥናትን ይመርጡ ነበር። ይህ "መምህር እከሌ" ለብዙዎች የመዘባበቻ ምክንያት በመሆንም "በቃ እንደ ህንዳዊ...መምህር ማስታወሻ ደብተር ቸክ አትበል" እየተባለ የቀልደኞች መሳሳቂያና መሳለቂያም ሆኖ ነበር።

ይህንን መምህር በተመለከተ አንባቢያን ብዙ ጥያቄዎችን ሊያነሱ ይችላሉ። የት/ቤቱ አስተዳደር ይህንን አያውቅም ነበር? ለምን ችላ ተብሎ ኖረ? በትምህርት ጉዳይ ተቆጣጣሪ የሆኑት በየደረጃው ያሉ መንግሥታዊ ተቋማትስ ስንፍናውን ሳይሰሙ ቀርተው ነው? ወዘተ." የሚሉት መጟገቻዎች መነሳታቸው አግባብ ነው። መልሱ እርግጥ ነው የተጠቀሱት አካላት በሙሉ ጉዳዩን ያውቁ ነበር። ችግሩ መምህሩ የት/ቤቱን ኃላፊዎችና የትምህርት አመራሮችን የሚይዝበት ዘዴና ብልሃት በጣም የረቀቀ ስለነበር "ጌታዋን የተማመነች በግ ላቷን ውጭ ታሳድራለች" እንዲሉ ማንም ሃይ ባይ ተቆጭ ሳይኖረው ከዳይሬክተሩ ባልተናነሰ ስልጣን እንደተፈራ መኖሩን ብዙዎች ያውቁ ነበር። ለብዙ አገራዊና ወቅታዊ ጉዳዮችም ቀድሞ የቤት ሥራው ይሰጥ የነበረው ለዚሁ መምህር እንደነበርም የማያውቅ አልነበረም። ምስክሮች በአካል ይፈለጉ የሚባል ከሆነም እማኞችን ወደ አካባቢው ሄዶ ማፈላለግ አይገድም።

አብዛኞቹ የኢትዮጵያ ፖለቲከኞች በሃምሳ ዓመት የአዲዮሎጂ ፍልስፍና ካልመራን እያሉ በአረጀ አስተሳሰብ ሙጭጭ ማለታቸው ከዚህ መምህር ጋር ሊያመሳስላቸው ይችላል። አንድም የዳዴ ተሽቀዳዳሚዎች መሆናቸው፣ ሁለትም ህልማቸውና ቅዠታቸው ሥልጣንና እርሱን ተከትሎ የሚመጣው ጥቅማ ጥቅም ውል ስለሚላቸው ሁሌም ከእዬዬያቸው ተገትተው አያውቁም። የወጣትነት አፍሮ ፀጉራቸው ብቻ ሳይሆን ርእዮተ ዓለማቸውም ሸብቶና ጎብጦ ከመቃብር አፋፍ ላይ መቆሙን እንኳን ባንነው ሊያስተውሉ አልቻሉም።

ተጨባጭ መከራከሪያ ይቅረብ ከተባለም በርካታዎቹ "የዳዴ ተሽቀዳዳሚ ፖለቲከኞች" ባለፉት ሦስት ዐሥርት ዓመታት ውስጥ ብቻ ጨቅላ አስተሳሰባቸው ግድ እያላቸው ለምን ያህል ጊዜያት አንዱን ቡድን በማክሰም ሌላ ቡድን እየፈጠሩ፣ እየተዋሃዱና እየተገነጣጠሉ ሲገለባበጡ እንደኖሩ ማስታወሱ ብቻ በቂ ይሆናል።


ፖለቲካቸውን እንደተጸየፈና በድኩምነታቸው እንደሚያዝንላቸው አንድ ዜጋ የጸሐፊው ምክር አንድና አንድ ብቻ ነው። ሃምሳ ዓመት በእንፉቅቅ ከመጓዝ ነፃ ወጥተው ለግላቸው ጥሞና ሱባዔ ይግቡ። ያረጀውን የፖለቲካ ርእዮተ ዓላማቸውንም ይጎንድሉና አዳዲስ ችግኞች እንዲበቅሉ ለወራሾቻቸው እድል ይስጧቸው።

እንኳን በፖለቲካ ዓላማቸው ተወዳድረው ሊያሸንፉ ቀርቶ ቋንቋቸው ራሱ ዘመን የሚመጥን ያለመሆኑንም ይረዱት። ቢቻላቸውና ቢሆንላቸው ከሚዲያ ፉከራና ቀረርቶ አደብ ገዝተው ራሳቸውን ይፈትሹ። በዳዴ እሽቅድምድም ተወዳድረው ለማሸነፍ የዘመኑ "ፈጣን ጎዳና" ስለማይመጥናቸው የሸንፈታቸውን የረጅም ጉዞ እየሰነዱ ቢያስነብቡን ለእነርሱም ለእኛም የሚበጅ ይመስለናል። "ልብ ያለው ልብ ያድርግ" አለ ይባላል የአገሬ አስተዋይ መካሪ። ሰላም ይሁን!

ኢኮኖሚ

# ንግድና ግብይት

# በኤክስፖርት ገበያው ቀዳሚው አረንጓዴ ወርቅ



**ፍሬሕይወት አወቀ**

ኢትዮጵያ ከምርቶቿ መካከል ጥቂት የማይባሉትን ለውጭ ገበያ በማቅረብ የውጭ ምንዛሬ ታገኛለች። በእዚህ የውጭ ምንዛሬም በአገር ውስጥ የማይመረቱና አስፈላጊ ምርቶችን እየገዛች ወደ አገር ውስጥ ታስገባለች።

ለእዚህ ግብይት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ከሚገኙት መካከል ቡና አንዱ ነው። ይህ አረንጓዴ ወርቅ እየተባለ የሚጠራው የውጭ ምርት ለኢትዮጵያ ዋነኛው የውጭ ምርት ሆኖ በርካታ አመታትን ዘልቋል። ይህን ተከትሎም «የኢኮኖሚ ዋልታ፣ የገቢ ምንጫችን» እየተባለ ተዘምሮለታል።

ለበርካታ ዓመታት ቡናን ለውጭ ገበያ በመላክ የምትታወቀው ኢትዮጵያ ከዓለም የቡና ዋጋ መውደቅና ከግብይት ሰንሰለት መንዛዛትና ህገወጥ ግብይት ጋር ተያይዞ ባለፉት አመታት ከዘርፉ እምብዛም ተጠቃሚ ሳትሆን ቆይታለች።

መንግስት ከምርቱ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት እንደ አንድ ስትራቴጂ ሲጠቀም የቆየው ብዙ ቡና መላክን ነበር። በዚህም ብዙ ቢሰራም ከግብይት ጋር ተያይዞ ያሉት እንደ ሰንሰለት መብዛትና ህገወጥ ግብይት ያሉት ችግሮች ከምርቱ የሚገኘው ገቢ የሚጠበቀውን ያህል እንዳይሆን አርገውት ቆይተዋል።

መንግስት ባለፉት አመታት ባከናወናቸው ተግባሮች ይህን ሁኔታ መቀየር ችሏል። ይህን ተከትሎም ከቡና የውጭ ንግድ የሚገኘው የውጭ ምንዛሬ እየጨመረ መጥቷል። ዘንድሮም ኢትዮጵያ በታሪኳ አይታው የማታውቀውን ውጤት በማስመዝገብ ከዘርፉ ሁነኛ ተጠቃሚ መሆኗ እየተገለጸ ነው። በአስር ወራት ውስጥ ብቻ ከአንድ ቢሊየን ዶላር በላይ ገቢ ከቡና የውጭ ንግድ መገኘቱም ይህንኑ ያመለክታል።

በበጀት ዓመቱ አስር ወራት ጊዜ ውስጥ የኢትዮጵያ ቡና በዓለም ገበያ በከፍተኛ ዋጋ መሸጡን የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን ከትናንት በስቲያ መግለጫ በሰጠበት ወቅት የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አዱኛ ደበላ አስታውቀዋል።

ዋና ዳይሬክተሩ ለዚህ ውጤትም ባለስልጣኑ በርካታ ተግባሮችን ማከናወኑን ይገልጻሉ። በኢትዮጵያ የቡና ኤክስፖርት ታሪክ በአስር ወራት ከአንድ ቢሊየን ዶላር በላይ መገኘቱን ጠቅሰው፣ ይህን ያህል ገቢ ሲገኝ በአገሪቱ ታሪክ የመጀመሪያው መሆኑንም ነው ያስታወቁት። ዋና ዳይሬክተሩ የቡና ዋጋ በውጭ ገበያ ከፍተኛ አፈጻጸም ማሳየት እንዲችል በቡና ዘርፍ ተሰማርተው በቀጥታ እንዲሁም በተዘዋዋሪ መንገድ አስተዋጽኦ ላደረጉ አካላትም ምስጋና አቅርበዋል።

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በ2013/14 በጀት አመት በመጀመሪያው ወር ላይ ዘርፉን ውጤታማ ማድረግ የሚያስችሉ ሥራዎችን አቅዶ ሰርቷል። በተለይም የውጭ ንግዱን ለማሳለጥ በቡና ልማቱና በግብይቱ ዙሪያ የሚስተዋሉ ችግሮች ተለይተው እርምጃ ተወስዶባቸዋል። በቁርጠኝነት ወደ ሥራው መግባት በመቻሉም በኢትዮጵያ የቡና ገበያ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ በበጀት ዓመቱ በአስር ወራት ብቻ አንድ ቢሊዮን 14 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ማግኘት ተችሏል።

በአስር ወራት ውስጥ 220 ሺ ቶን ለመላክ አቅደው 232 ሺ ቶን ቡና ወደ ውጭ ገበያ በመላክ በመጠን ከ105 በመቶ በላይ አፈጻጸም ማስመዝገብ ተችሏል። በገቢ ዕቅዱም እንዲሁ 810 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ለማስገባት ታቅዶም አንድ ቢሊዮን 14 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ተገኝቷል፤ አፈጻጸሙም የእቅዱ 112 በመቶ ነው። ይህም ካለፈው በጀት ዓመት ጋር ሲነጻጸር፣ በመጠን 40 በመቶ በገቢ ደግሞ 62 በመቶ ብልጫ የተመዘገበበት ነው።

በሚቀጥሉት ሁለት ወራትም ከሶስት ሚሊዮን ዶላር በላይ ለማግኘት እየተሰራ መሆኑን ዶክተር አዱኛ ጠቅሰው፣ በአጠቃላይ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በድምሩ ከአንድ ነጥብ ሁለት እስከ አንድ ነጥብ ሶስት ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ከቡና ብቻ ማግኘት እንደሚቻል አብራርተዋል።

ይህ ገቢም ኢትዮጵያ በአስር ወራት ውስጥ አጠቃላይ በውጭ ገበያ ካገኘችው ገቢ ጋር ሲነጻጸር 30 በመቶ የሚሆነውን ይሸፍናል ሲሉ ገልጸው፣ ከግብርናው ዘርፍ ጋር ሲነጻጸር ደግሞ 50 በመቶ ያህሉን ይሸፍናል ብለዋል።

ኢትዮጵያ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ በቡናው ዘርፍ ከፍተኛ ውጤት ለማስመዝገቧ የተለያዩ ምክንያቶች መኖራቸውን ዋና ዳይሬክተሩ ጠቅሰው፣ ውጤት ለማስመዝገብ ባለስልጣኑ ካከናወናቸው ተግባሮች መካከል በግብይት ሰንሰለት ውስጥ ያሉትን ችግሮች ነቅሶ ማውጣት አንዱ መሆኑን አስታውቀዋል። በተለይም በቀጥታ ትስስር አርሶ አደሮችንና አቅራቢዎች ምርታቸውን በቀላሉ መቀባባል እንዲችሉ መደረጉን ተናግረዋል።

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ማብራሪያ፤ ጥራቱን የጠበቀ ቡና በመጠንም እንዳይባክን አርሶ አደሮች ለአቅራቢዎች፤ አቅራቢዎች ደግሞ በቀጥታ ለላኪዎች ማስረከብ እንዲችሉና ላኪዎችም ዱካውን ተከትለው መለየትና ማወቅ የሚቻል ምርት ለዓለም ገበያ ማቅረብ የሚያስችላቸውን ስርዓት በመዘርጋት የኢትዮጵያ ቡና በተሻለ ዋጋ በዓለም ገበያ ላይ እንዲሸጥ ተደርጓል።

እያንዳንዱ ባለድርሻ አካል በቁርጠኝነት መሥራት በመቻሉ የተገኘ ውጤት ስለመሆኑ ያነሱት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በተለይም በግብይት ሥርዓት ውስጥ የነበሩ ለኤክስፖርቱ ማነቆ ሆነው የቆዩ አሰራሮችን በመፈተሽ በማስተካከልና በተለይም የኮንትሮባንድና ህገወጥ ንግድን በሶፍትዌር በመከታተል ውጤት መመዝገቡን ተናግረዋል። ቡና ጭነው ከመንገድና ከመሥመር የሚወጡ ባለሃብቶች እንዲሁም ተሽከርካሪዎች ላይ እርምጃ በመውሰድ የኮንትሮባንድ መጠኑ እንዲቀንስና ቡና ወደ ዓለም ገበያ በቀጥታ እንዲገባ ተሠርቷል ሲሉም ያብራራሉ። በተጨማሪም እምነት በመፍጠር ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር የተሰራው ሥራ ለተመዘገበው ውጤት የጎላ ድርሻ እንዳለውም ነው ዋና ዳይሬክተሩ ያመለከቱት።

ዋና ዳይሬክተሩ እንዳሉት፤ በአሁኑ ወቅት ያለው የዓለም የቡና ገበያ ለገቢው መጨመር ሌላው ምክንያት ነው። ይህም ለተገኘው ገቢ 20 በመቶ ድርሻ አለው ይላሉ። ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ የቡና አቅርቦት መጠን መጨመሩ ሲሆን ይህም ከ70 በመቶ ድርሻ በላይ ነው። ሌሎች የጊዜና የጥራት ሁኔታዎችም የራሳቸው ድርሻ አላቸው። አሁን ላይ ለተገኘው ውጤት የአንበሳውን ድርሻ የሚይዙት የአቅርቦት መጠን መጨመርና የዓለም ቡና ገበያ ዋጋ መጨመር ናቸው።

የስፔሻሊቲ ቡና በድርድርና በስምምነት፤ የኮሜርሻል ቡና ደግሞ በጨረታ የሚሸጥ መሆኑን የጠቀሱት ዋና ዳይሬክተሩ፤ የዓለም የቡና ዋጋ መጨመር ጠቀሜታው ለኮሜርሻል ቡና እንደሆነ አስረድተዋል። በመሆኑም በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ቡና ወደ ስፔሻሊቲ ቡና ገበያ በመሸሸ በየጊዜው የሚቀያየረውን የዓለም የቡና ዋጋ ለመቋቋምና የተሻለ ምርት በተሻለ ዋጋ ለማቅረብ እየተሠራ መሆኑን አስረድተዋል።

ለዚህም የዛሬ ሁለት ዓመት ይህን ስትራቴጂ በመያዝ ወደ ሥራው መግባት መቻሉን ጠቅሰው፣ በተለይም በአሁኑ ወቅት 60 በመቶ የሚደርሰው የኢትዮጵያ ቡና በስፔሻሊቲ ገበያ የሚሸጥ መሆኑን ገልጸዋል። 40 በመቶ የሚያህለው ቡና ደግሞ በኮሜርሻል ገበያ ይሸጣል ይላሉ። ይህ አይነቱ ግብይት በየጊዜው የሚቀያየረውን የዓለም የቡና ገበያ ዋጋን ለመቋቋም እንደሚያስችል ተናግረው፣ ወደ ስፔሻሊቲ ቡና ገበያ በስፋት መግባት እንደሚያስፈልግ ዋና ዳይሬክተሩ አስገንዝበዋል።

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ማብራሪያ፤ በአሁኑ ወቅት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ በተጠና መልኩ ከኮሜርሻል ይልቅ ወደ ስፔሻሊቲ ቡና ኤክስፖርት ሽግግር እየተደረገ ነው። ይህም አሰራር በየጊዜው እየተቀያየረ የሚገኘውን የዓለም የቡና ዋጋ ለመቋቋም እንዲሁም ጥራት ያለው ቡና በማቅረብ የተሻለ ገቢ ማግኘት እንዲቻል አድርጓል። በግብይት ውስጥ ያሉ ማነቆዎችን መፍታት እና የቀጥታ ትስስር ተግባራዊ መደረጉም ለተገኘው ገቢ ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክተዋል።

የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን የገበያ ልማትና ቁጥጥር ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሻፊ ኡመር በተለይ ለጋዜጣው ሪፖርተር እንዳሉት፤ የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ግብይቱን የማዘመንና ፍትሃዊ የማድረግ እንዲሁም እሴት የመጨመር ተግባርን በማከናወን አገሪቷ ከዘርፉ የተሻለ የውጭ ምንዛሪ እንድታገኝ ግብ ይዞ እየሠራ መሆኑን ይገልጻሉ። አጠቃላይ ግቡን ሊያሳኩ የሚችሉ ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛሉ ብለዋል።

የኢትዮጵያ ቡና በአሁኑ ወቅት ላስመዘገበው ውጤት ምርቱ ሳይባክን ከምርት እስከ ኤክስፖርት መዳረሻ ድረስ በትክክል መውጣት የሚያስችለውን ሥራ መሥራት መቻሉ እንደሆነ ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ይገልጻሉ፤ በአሁኑ ወቅት ከዘርፉ ከፍተኛ ውጤት መመዝገብ እንዲችል በርካታ ሥራዎች መሠራታቸውንም አስታውሰዋል።

ባለስልጣኑ ከሠራቸው ሥራዎች መካከልም አንደኛው አገራዊ ግብረ ሃይልን የማጠናከር ሥራ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደራሽ ቁጥጥር በማድረግ ቡና እንዳይባክን ማድረግ ተችሏል። ሶስተኛው በሶፍትዌር ሲስተም በመገንባት ሁለቱን በመደገፍ ቡናው ሳይባክንና ከመጣበት ቦታ በቀጥታ ወደ መዳረሻው እንዲደርስ የማድረግ ሥራ ነው።

ከግብረሃይል አንጻር በተለይም ከፌዴራል ፖሊስ፤ ከጉምሩክ ኮሚሽን፤ ከአዲስ አበባ ከንግድ ቢሮ፤ ከኦሮሚያ፣ ከደቡብ ምዕራብና ከሲዳማ ብሔራዊ ክልል መንግሥት ጋር በጋራ በመሆን የተጠናከረ የቅንጅት ኮሚቴ በማዋቀር ኮሚቴዎቹም ከታች ያሉትን ግብረሃይሎች በማጠናከር ትርጉም ያለው ሥራ ተሰርቷል። በቁጥጥርና ክትትል ሥራውም ህገወጥ ነጋዴዎችን በመቅጣት አጠቃላይ ከ83 ሚሊየን ብር በላይ በቅጣት ገቢ ማግኘት ተችሏል።

እስካሁን በነበረው አሠራር የኢትዮጵያ ቡና ግብይት የላላ ቁጥጥር የነበረውና በትክክልም ቡናው የት እንደደረሰ የማይታወቅበት ሁኔታ እንደነበር ያስታወሱት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ በተለይም በምርት ገበያ ላይ ኮንትሮባንዱ በዝቶ ቡናው ወደ አገር ውስጥ ይመለስ እንደነበርም አስታውሰዋል። በአሁኑ ወቅት ባለስልጣኑ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን ማከናወኑን ተከትሎ ችግሮችን ማቃለል ችሏል ይላሉ። የጥራትና ቁጥጥር ሶፍትዌሮችን በመገንባት የአገሪቷ ቡና የት እንደሚገኝ፤ ከየት እንደተሰበሰበና የት እንደደረሰ በመከታተል እርምጃ እየወሰደ ይገኛል ብለዋል።

በዚህም መሰረት 18 የሚደርሱ ቡና የጫኑ መኪኖች ቡናውን የት እንዳደረሱ ያልታወቁ ከተመረተበት ቦታ አንስተው ወደ ኤክስፖርት ማዘጋጃና ማከማቻ ያላደረሱ መሆኑ ተጠርጥሮ ከፌዴራል ፖሊስ ጋር በመሆን በቁጥጥር ስር እንዲውሉ መደረጉን ይገልጻሉ። ከእነዚህም መካከል ስድስት የሚደርሱ ተሽከርካሪዎች 77 ቶን የሚደርስ ቡና በመሰወራቸው ማስረጃ ተገኝቶባቸው በቁጥጥር ሥር እንደሚገኙም ጠቁመዋል።

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ እንደገለጹት፤ የቡና ህገወጥ አሰራርን ለመከላከል በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በገበያ ልማትና ቁጥጥር ዘርፍ ዘርፈ ብዙ ሥራዎች እየተሠሩ ሲሆን፣ በተለይም ህገወጦችን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ የተለያዩ ስልቶች ተቀይሰው ተግባራዊ እየተደረጉ ናቸው። በተለይም ህገወጦችን ለመቆጣጠር የሚያስችል ሶፍትዌር እንዲበለጽጉ ተደርጎ ወደ ሥራ ከተገባ በኋላ ህገወጥ አሰራሮች ቀንሰዋል፤ ህገወጦችንም በቀላሉ ለይቶ ለመያዝ ተችሏል።

የኢትዮጵያ ቡናን በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ ሆኖ መዝለቅ እንዲችል በጥራት ከማምረት ባለፈ ገበያ ውስጥ ሰብሮ ለመግባት ሁለት ስትራቴጂዎችን ተቀርጸው እየተሰራ መሆኑን ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ጠቅሰው፤ አንደኛ ነባር የገበያ መዳረሻዎች የሆኑትን አውሮፓ አገራትን ጨምሮ በዋናነት በሰሜን አሜሪካ፣ በደቡብ ኮርያ፣ በጃፓን፣ ጀርመንና በጣሊያን ገበያ ውስጥ መቆየት መሆኑን አስታውቀዋል። በሁለተኛው ስትራቴጂ መሰረት ደግሞ የኢትዮጵያ ቡናን በማስተዋወቅ የተሻለ ገበያ ለማግኘት አዳዲስ የገበያ መዳረሻዎች የማፈላለግ ሥራ በስፋት እንደሚሠራም ገልጸዋል። በአሁኑ ወቅትም ቻይና እና ታይዋን አዳዲስ የገበያ መዳረሻ እየሆኑ መምጣታቸውን ጠቅሰው፣ በቀጣይም በዚህ ላይ እንደሚሰራ ገልጸዋል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## ፈቅዶ መታመም

ዋስልኝ አየለ

አሜሪካ ወይም አውሮፓ አገራት መኖር የምመኘው የተደላደለ ኑሮ ለመኖር አይደለም። ፒዛና በርገር ለመብላት ወይም ፈጣን የቴክኖሎጂ አማራጮችን ለመጠቀም አይደለም። ከዚህ በላይ የሚያጓጓኝ ንጹህ አየር መተንፈስ ነው። የዓለም ምርጥ የአየር ንብረት ያላት አገር ውስጥ ሆኖ፣ ተፈጥሮ ያደላላት የሚመስል ምቹ የተፈጥሮ ሀብት ያላት አገር ውስጥ ሆኖ፤ በሰው ሰራሽ ዓለም ውስጥ የሚኖሩ አገራትን አየር መናፈቅ ምንኛ መረገም ይሆን?

ደፈር ብለን እንናገረው ከተባለ ለዚህ ሁሉ የዳረገን መሃይምነት ነው። መሃይምነት ሲባል መጻፍና ማንበብ የማይችል ማለት አይደለም፤ ዲግሪ የደራረበ ብዙ መሃይም አለና።

የሰሞኑ የአየር ሁኔታ ነፋስና ፀሐይ የበዛበት ነው፤ በኢትዮጵያ የአየር ሁኔታ ይህ የተለመደ የግንቦት ወር ባህሪ ነው። ተፈጥሯዊ ክስተት ነው።

አደገኛ የሆነው ግን ይህ ሳይሆን በሰው ሰራሽ መንገድ ያበላሸናቸው ነገሮች ናቸው። ከተፈጥሯዊው የአየር ሁኔታ ጋር ተዳምሮ ብዙ ሰዎች ሰሞኑን ጉንፋን ተይዘዋል። ጉንፋን ቀላሉ ነው፤ ብዙ ሰው የአስም ህመምተኛ ነው። ይህ ሁሉ የሚሆነው በቆሻሻ በሚፈጠር መጥፎ ሽታ ነው።

አዲስ አበባ ውስጥ አፍንጫ ሳይያዝ የሚታለፉ ወንዞች የሉም። ቱቦ ባለበት ቦታ ያለፈ ሁሉ ጉንፋን ተይዞ ወይም ከፍተኛ የራስ ምታት አጋጥሞት ነው የሚያልፍ። ድልድዮች ባሉበት ሁሉ አጻያፊ ነገር እያዩ ማለፍ የተለመደ ሆኗል። በየቦታው ሽታ አለ። ይህ ወቅት ደግሞ ከፍተኛ ነፋስና ፀሐይ ያለበት ስለሆነ ለብዙ በሽታዎች አጋላጭ ነው። የዝናብ ወቅት ሲሆን ቢያንስ ዋና ዋናውን ዝናብ ሊያጥበው ይችላል፤ ሽታውም የከፋ አይሆንም።

ይሄ ሁሉ የሆነው እንግዲህ በግንዛቤ ማጣት ነው። በሰው ሰራሽ መንገድ ነው እየታመምን ያለነው። የጽዳት ባህላችን ደካማ ነው። የዕለት ከዕለት ሥራ መሆን የሚገባውን ጽዳት፣ በዘመቻ ነው የምናጸዳው።

ብዙ ነገሮችን የምናደርገው ዓመት ጠብቀን ነው። ለምሳሌ ዕቅድ የምናወጣው አዲስ ዓመት (መስከረም) ሲደርስ ነው። መስከረም ካለፈ በኋላ፤ እንኳን አዲስ ዕቅድ ማውጣት የታቀደውም ይረሳል። የበጎ አድራጎት ሥራዎችን (ለምሳሌ ህሙማንንና አቅመ ደካሞችን መርዳት) የምንሰራው እንደ እንቁጣጣሽ፣ ገና፣ ፋሲካ፣ መውሊድ ወይም አረፋ ያሉ በዓላት ሲመጡ ነው። እነዚህ በዓላት ሲያልፉ ይረሳል።

ብዙ ነገሮችን የምናደርገው አሁንም ሁነት ጠብቀን ነው። ለምሳሌ ከተሞች የሚጸዱት በከተማዋ ውስጥ የሆነ ዝግጅት የሚደረግ ከሆነ ነው። ለምሳሌ የብሔር ብሔረሰቦች ቀን፣ የከተሞች ሳምንት ወይም ሌላ መንግስታዊም ሆነ ሕዝባዊ በዓላት የሚደረጉ ከሆነ የዚያን ሰሞን ቀለሞች ይቀባሉ፤ ቆሻሻዎች ይጸዳሉ። ያ ዝግጅት ሲያልፍ ግን አይቀጥልም፤ እንዲያውም ይባስ ብሎ በዝግጅቱ ምክንያት የወዳደቁ ተረፈ ምርቶች የሚያቆሽሹት ይበልጣል።

በየዓመቱ ‹‹ህዳር ሲታጠን›› እየተባለ በየቦታው ቆሻሻ ይቃጠላል (ሌላ ቀን አይደረግም እንጂ)፤ ዋና ዓላማውም ቆሻሻን ማቃጠልና ጽዱ አካባቢ መፍጠር ነው።

እንዲህ አይነት አጋጣሚዎች የማንቂያ ምክንያት ይሆኑናል። ቢያንስ በእንዲህ አይነት አጋጣሚ እንኳን አስታውሰን መነቃቃት ቢፈጠር ማለት ነው። ልቦና ቢሰጠን ደግሞ በዚያው ቢለምድብን ጥሩ ነበር፤ ግን አልሆነም።

በነገራችን ላይ በዓመት አንዴ የሚደረገው ህዳር ሲታጠን እንኳን በዕለቱ የሚኖረው የቆሻሻ ማቃጠል ራሱን ችሎ ሌላ ብክለትም ሲሆን ይታይ ነበር። ከንጹህ አየር ፍለጋ ባህላችን ይልቅ ባህላዊ ለሆነው ልማድ ተብሎ ነበር ማለት ነው።

ቆሻሻ ጭስ የወጣውም የማጽዳት ሥራው የዚያን ዕለት ብቻ ስለተሰራ ነው። ሁሌም የሚጸዳ ቢሆን ኖሮ እንዲያ የሚያጥለቀልቅ ጭስ ባልኖረ ነበር። ሰዎች ቆሻሻውን ሲያቃጥሉ የዚያን ቀን ብቻ ማድረግ የሚቻል ነው የመሰላቸው። ይሄ ማለት ዋና ዓላማው ቆሻሻን ማስወገድ ሳይሆን ባህል ስለሆነ ብቻ የወጉን ለማድረስ ነበር ማለት ነው።

በነገራችን ላይ አዲስ አበባ ንጹህ የምትሆነው በማጽዳት ሳይሆን ባለማቆሸሽ ነው። የከተማዋ ነዋሪ በነቂስ ወጥቶ ሁሉንም ቆሻሻ ጠራርጎና አጽድቶ ቢገባ የአስተሳሰብ ለውጥ ከሌለ በአንድ ቀን ሊበለሻሽ ይቻላል።

የወንዝ ዳርቻዎች እኮ ጥሩ ምሳሌ ይሆኑናል። በክረምት ጎርፍ ጠራርጎ ሲወስደው ወንዙ ንጹህ ይሆናል፤ ወዲያውኑ ግን ረፋድ እንኳን ሳይሆን አፍንጫ ተይዞ የሚታለፍበት ይሆናል። በግንብ እና በአጥር ዙሪያ ያለው አፍንጫ የሚበረቅስ መጥፎ ሽታ አብሮ የተገነባ አልነበረም፤ በሰዎች ሽንት እና የቆሻሻ መጣያነት ነው እንዲያ የሚሆነው።

መቼም እንግዲህ ገና ለገና ይቆሸሻል ተብሎ ዝም መባል የለበትም። የሚያቆሽሸውን ያህል በዚያው መጠን ደግሞ ቶሎ ቶሎ የሚያጸዳ ቢኖር ችግሩ ይቀንሳል። ልብ ብላችሁ ከሆነ ብዙ ጊዜ ሽንት የሚሸናው ከዚህ በፊት የተሸናበት ቦታ ላይ ነው፤ ቆሻሻ የሚጣለው ቆሸሾ የሚታይ ቦታ ላይ ነው። የያዝነውን ሶፍት እንኳን ንጹህ ቦታ ላይ ለመጣል ይከብደናል። ቆሻሻ ቦታ ከጠፋ ብዙ ሰው ሊጥለው ያሰበውን ነገር በኪሱ ይከተዋል፤ ቆሻሻ ያለበት ቦታ ለመጣል ማለት ነው። እንግዲህ ከዚህ የምንረዳው ሁሉም አካባቢ ንጹህ ቢሆን ሁሉም ለንጽህና እንደሚበረታታ ነው።

የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ ልብ ብላችሁ ታውቃላችሁ? ምንም እንኳን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የቀረ ቢሆንም የፕላስቲክ ውሃ የታሸገበትን ወረቀት ለመጣል ዘወር ዘወር ብለው ያያሉ። የተጣለ ካለ ሁሉም ይጥላል። የተጣለ ከሌለ ግን ፕላስቲኩ ወገብ ላይ ካለው ሽፋን ውስጥ ሽጎጥ ያደርጉታል፤ ወይም ኪሳቸው ይከቱታል (እኔ ብዙ ቀን ኪሴ ከትቻለሁ)። መሬት ላይ በመጣል የሚጀምረው አንድ ሰው ነው ማለት ነው፤ ከዚያ በኋላ መቼም አንዴ ተጥሎበታል በሚል ሁሉም እየጣለ ወለሉ የፕላስቲክ ፋብሪካ ይመስላል። ለምሳሌ አነሳሁት እንጂ የውሃ ፋብሪካዎች አሁን የመክደኛውን መሸፈኛ አስቀርተውታል።

እነሆ ይህ በዘመቻ ብቻ የሚደረግ የጽዳት ባህላችን ለውጥ ሳያመጣ ቀርቶ በእንዲህ አይነቱ ነፋስና ፀሐይ በሚበዛበት የግንቦት ወር ጉንፋን በጉንፋን ሆነናል። በእንዲህ አይነቱ ወቅት ይብስበታል ለማለት እንጂ የመጥፎ ሽታዎች ነገር ከዓመት ዓመት ነው። በመንደሮች መካከል ባሉ የውስጥ ለውስጥ ቦዮች ሁሉ መጥፎ ሽታ አለ።

የሚያሳዝነው ግን የተማረና የሰለጠነ የሚባል ሰው ባለበት ሁሉ እንዲህ አይነቱ አስነዋሪ ነገር የሚታይ መሆኑ ነው። ይሄ በትልልቅ የፌዴራል ተቋማት ውስጥ ሳይቀር የታዘብኩት ነው። በእንደዚያ አይነት ተቋም ውስጥ ቢያንስ መጻፍና ማንበብ የማይችል የለም፤ በብዛት ደግሞ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው ነው። ምንም እንኳን ጥፋቱን የሚፈጽመው ጥቂት ሰው ሊሆን ቢችልም መጸዳጃ ቤት ውስጥ የሚታየው ነገር ከላይ እስከ ታች ምን ያህል ኋላቀር እንደሆንን ያሳያል።

ጽዳት በዘመቻ ብቻ አይሁን! ዓመታዊ በዓላትን ወይም የመንግሥት ባለሥልጣን የሚያስጀምረውን ዘመቻ ብቻ ተከትሎ ከማድረግ ወጥተን የዕለት ከዕለት ሥራ ይሁን፤ አዲስ አበባን ንጹህ ማድረግ የሚቻለው በማጽዳት ብቻ ሳይሆን ቆሻሻን ያለቦታው ባለመጣል ነው!

# ዓለም አቀፍ



## ኤልሳቤት ቦርን የፈረንሳይ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው ተሾሙ


አዲስ አበባ፣ ኤልሳቤት ቦርን በ30 አመታት ውስጥ የመጀመሪያዋ የፈረንሳይ ሴት ጠቅላይ ሚኒስትር በመሆን በፕሬዚዳንት ኢማኑኤል ማክሮን ተሾመዋል።

በአገሪቱ የሰራተኛ ሚኒስትር የነበሩት ኤልሳቤት ቦርን÷ የ61 አመቱን የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር ዣን ካስቴክስን ተክተው የፈረንሳይ ጠቅላይ ሚንስትር ሆነው መሾማቸው ተሰምቷል።

ተሰናባቹ የፈረንሳይ ጠቅላይ ሚኒስትር ዣን ካስቴክስ የፕሬዚዳንት ማክሮን ዳግም መመረጥን ተከትሎ ለአዲሱ መንግስት የለውጥ አካል ለመሆን በሚል ስልጣናቸውን በገዛ ፈቃዳቸው መልቀቃቸውን አናዶሉ ዘግቧል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ቦርን ከስነምህዳር ፣ ከጤና፣ ከትምህርት፣ ከዴሞክራሲ እና ከደህንነት ጋር በተያያዘ ከአዲሱ የአገሪቱ አስተዳደር ጋር ትኩረት ሰጥተው እንደሚሰሩ ገልጸዋል።

የቦርን በጠቅላይ ሚኒስትርነት መሾም በአብዛኛዎቹ የመንግስት ደጋፊዎች ድጋፍ የተቸረው ሲሆን በተፎካካሪ ፓርቲዎች በኩል ግን ተቃውሞ ማስተናገዱ ታውቋል።



## ሩሲያ የስዊዲንና ፊንላንድ የኔቶ አባል መሆን እንደማያሳስባት ገለጸች

አዲስ አበባ፣ ግንቦት 8፣ 2014 (ኤፍ ቢ ሲ) ሩሲያ የሚያሳስባት የስዊዲንና ፊንላንድ የኔቶ አባል መሆን ሳይሆን አገራቱ ኔቶ ወታደራዊ መሰረተ ልማቱን እንዲያስፋፋባቸው የሚፈቅዱ ከሆነ ነው አሉ ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን።

የሩሲያ ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን ሞስኮ በተካሄደው የጋራ የፀጥታ ስምምነት ድርጅት መሪዎች ጉባኤ ላይ ባስተላለፉት መልዕክት÷ የፊላንድ እና የስዊድን የኔቶ አባል መሆን የሩሲያ ስጋት አይደለም ብለዋል።

ሆኖም “አገራቱ የሰሜን አትላንቲክ ጦር ቃል ኪዳን ድርጅት (ኔቶ) ወታደራዊ መሰረተ ልማቱን እንዲተክልባቸው የሚፈቅዱ ከሆነ ግን ያ ምላሽ እንድንሰጥ የሚያስገድደን ስጋት ይሆናል” ነው ያሉት።

ሩሲያ የምትሰጠው ወታደራዊ ምላሽም በስዊዲንና ፊንላንድ ኔቶ የሚያደርገው ወታደራዊ እንቅስቃሴ ይወስነዋልም ብለዋል ፕሬዚዳንቱ።

ፊንላንድ እና ስዊዲን ለዓመታት የነበራቸውን የገለልተኝነት አቋም በመተው የኔቶ አባል ለመሆን መወሰናቸውን አስታውቀዋል።

# ባለውለታዎቻችን

# አሉላና ስላልተነገሩት ውለታዎቻቸው አንዳንድ ነጥቦች

ግርማ መንግሥቴ

አገር ስራዬ ብላ ካፈራቻቸው ማንነቶች፤ ስራዎቻቸው በአግባቡ ለትውልድ ያልተላለፉላቸው ብሔራዊ አርበኞች፣ አቻ የለሽ ጀግኖች ብዙዎች ናቸው። ከጀግኖቹም መካከል ቀዳሚዎች ያሉ ሲሆን አንዱም በ "አይበገሬው ጀነራል"ነቱ (ዶጋሊው ላይ ባስገኘው ድል ምክንያት ያገኘው መጠሪያ ነው) የሚታወቀው፤ ታሪክ ፀሀፊዎቹ እነ በርክሌይ ሳይቀሩ "ከአፄ ቴዎድሮስ ሞቱ በኋላ አቢሲኒያ ያፈራችው ታላቅ መሪ"፤ ባለ ውለታነታቸውም እንደዛው። ፕሮፌሰር መርዕድ ወልደ አረጋይ "Alula, Dogali and Ethiopian Unity" በሚል ጽሁፋቸው "ከአሳዛኙ የአፄ ቴዎድሮስ የመቅደላ ፍፃሜ በፊትም ሆነ በኋላ አፄ ቴዎድሮስን የመሰለ አንድ ሰው ቢኖር አሉላ አባ ነጋ ብቻ ናቸው፡፡" በማለት ምስክርነታቸውን የሰጡላቸው ያሉለት አሉላ አባ ነጋ ናቸው።

ደራሲያ፣ የታሪክ ጸሐፍት፣ የኪነጥበብ ባለሙያዎች፣ የሀይማኖት አባቶች፣ ስነቃላችን ... ስንትና ስንት ጀግኖቻችንን ሲያነሱ፣ ሲያወድሱ፣ ሲያሞግሱና ለትውልድ ሲያቀብሉ የኖሩ (ይህ የሚቀጥል ይሆናል) ሲሆን አንዱና ቀዳሚውም አሉላ እንግዳ (በፈረስ ስማቸው አሉላ አባ ነጋ) ናቸው።

የውጪዎቹ (ጠላቶቻችን ሳይቀሩ) ጥናትና ምርምር አድራጊዎች፣ የፖለቲካል ሳይንስ አጥኚዎች፣ የታሪክ ፈልፋዮች ስለ ስመ ጥር ኢትጵያዊያን ያላነሱት የሌለ ሲሆን፤ አንዱም የቀይ ባህሩ አንበሳ፣ የዶግዓሊው ጦርነት (ጥር 26፣ 1887) ባላምባራስ፣ የራስ አሉላ አባ ነጋ ሕይወትና ስራ ነው። (በዋናነት የሚጠቀሱት ሁለት ዓበይት ጦርነቶች ደግሞ የ1875 የጉንደት እና የ1876 የጉራዕ ጦርነቶች ናቸው፡፡) ለመነሻና ማስታወሻ ያህል የሚከተለኩትን (ከዘሪሁን አበበ ይግዛው የተዋስናቸውን) ሁለት አንቀፆች እንመልከት፤

በ1805 የኦቶማን ቱርክ የግብፅ አስተዳዳሪ ሆኖ የተሾመው አልባኒያዊው ሙሐመድ ዓሊ ወደ አፍሪካ መምጣት ለብዙ ክስተቶች ምክንያት ሆኗል፡፡ [...] ከ1805 እስከ 1849 ስልጣን ላይ የቆየው ሙሐመድ ዓሊ በዋናነት የተሳካለት ግብፅ ራሷን የቻለች እና ከኦቶማን ቱርኮች ነፃ የሆነች አገር መመስረቱ ነው፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ ቀደም ሲል የኦቶማን ግዛቶች የነበሩ የቀይ ባህር እና የህንድ ውቅያኖስ አዋሳኝ ጠረፎችንም በግብፅ ስር ለማድረግ ጥሯል፡፡ [...] ዋና እና የከረሩ ጦርነቶች የተካሄዱት ግን የሙሐመድ ዓሊ የልጅ ልጅ ኬዲቭ እስማኤል ፓሻ (1863-1879) ወደ ስልጣን መምጣትን ተከትሎ ነበር፡፡

የአያቱን የመስፋፋት ሃሳብ ለማሳካት ደፋ ቀና ብሎ፤ ብዙ ደክሞ እና በአሜሪካውያን እና በአውሮፓውያን በአማካሪዎች እና በቅጥረኛ ወታደሮች ታጅቦ ኢትዮጵያን ለመውረር ቆርጦ የነበረው ኬዲቭ ኢስማኤል ፓሻ ዓላማው ከግዛት ማስፋፋት [ያ]ለፈ ነበር፡፡ [...] በዋናነት የሚጠቀሱት ሁለት ዓበይት ጦርነቶች ደግሞ የ1875 የጉንደት እና የ1876 የጉራዕ ጦርነቶች ናቸው፡፡ በሁለቱም ጦርነቶች ወራሪዎቹ ግብፆች እና አጋዥ ቅጥረኛ ወታደሮች እና አማካሪ ጄኔራሎች ሽንፈትን ተጎንጭተው ተመልሰዋል፡፡ ድልም ለኢትዮጵያ እና ለኢትዮጵያውያን ሆነ፡፡ ከእነዚህ ሁሉ ድሎች በስተጀርባ ደግሞ የአንድ ሰው ስም ሁሌም በጉልህ ይነሳል፡፡ አሉላ አባ ነጋ!!

የአለም አገራት መሪዎች ጀግኖቻችንን ጨምሮ በስመጥር ኢትዮጵያዊያን ሲደመሙና ሲበሳጩ ስለ መኖራቸው ምንም አይነት ጥርጣሬን የማያጭር እውነታ ሲሆን፤ ለዚህም ለአሉላ ከጀነራልነት የዘለለ ማእረግን የሰጠችው እንግሊዝ ተጠቃሽ ነች።

በሰሜኑ የአገራችን ክፍል ያልተካሄደ የጦርነት አይነት የለም። እኛን ለመድፈር በዛ በኩል ያልመጣም የለም። ሊውጠን ያላሰፈሰፈም በጭራሽ የለም። አይኑር እንጂ ሁሉም ምሱን እያገኘ ያልተመለሰ የለም። ለመጣው ፋሺስት ሁሉ ምሱን ሲሰጡት ከኖሩት መካከል ደግሞ አንጋፋው የጦር አበጋዝ አሉላ አባ ነጋ ናቸው።

ኢትዮጵያዊያን አርበኞች የተጋረጡባቸውን አደጋዎች ከመመከትም ባለፈ በማክሸፍ፤ ሲጋልብ የመጣን የውጪ ጠላት በመደምሰስና በመቅበር በኩል አለም ያውቃቸዋል። እነዚህ ዘመን ተሻጋሪ ድሎች ደግሞ ሁሉም በሚባል ደረጃ በጊዜና ቦታ የሚገለፁ ሲሆን፤ ከእነዚህም መካከል፣ ልክ እንደ አድዋ (1888 ዓ.ም) ሁሉ፣





ጉንደት እና ጉርአ ተጠቃሾች ናቸው። ይሁኑ እንጂ እነዚህ ለአሉላ ግን ብቸኞቹ የድሎቹ ስፍራዎች አይደሉም።

ድሎች ሁሉ ያለ አሉላ እና ጦራቸው የሚታሰቡ አይደሉምና አስፈላጊ ከሆነ ግብፆችን ዋቢ አድርጎ መነጋገር ይቻላል። መልሳቸው "ጀግናው አሉላ አባ ነጋ!!!" እንደሚሆን ቢታወቅም፤ "ማን ነው አይቀጡ ቅጣት የቀጣችሁ?" ብሎም መጠየቅም ይቻላል። ከቱርኮቹስ አንፃር??

"ቱርኮች ምጽዋን መያዛቸውን የሰሙት አጼ ዮሐንስ የጦር አዛዣቸው ለነበሩት ራስ አሉላ 'እስከመጣ ድረስ ተጨማሪ ቦታ እንዳይዙ ነቅታችሁ ጠብቁ' ብለው መልዕክት ላኩ[።] ራስ አሉላ ግን 'ለጌታ ድግስ እንጂ ጦር አያቆዩትም' ብለው ቱርኮችን ተዋግተው ድል አረጉ፡፡" ተብሎ በአገር ውስጥም ሆነ በውጪው ሲያስተጋባ የነበረውን የአሉላን የጦር ሜዳ ውሎና ፍፁም ኢትዮጵያዊ ጀግንነት እዚህ አሰብ አድርጎ ማለፉ ስለ ውለታቸው ሲባል ተገቢ ይሆናልና አድርገን ብናልፈው አይከፋም።

ማሞ ውድነህ በ1847 በተምቤን ዙቁሊ ሚካኤል መወለዳቸውን የመዘገቡላቸው አሉላ አባነጋ ተዋጊ አርበኛ፣ ማራኪ ጦረኛ ብቻ አይደሉም። አሉላ የጦር መሪ ብቻም አይደሉም። አሉላ ማራኪ አንበርካኪም ብቻ አይደሉም። ታሪካቸው እንደሚያስረዳው አሉላ አባ ነጋ ሁሉንም ነበሩ። የተዋጣለት አስተዳዳሪ፣ የተሳካለት መፍትሄ አመንጪ፣ ይህ ቀረሽ የማይባሉ ዲፕሎማት፤ .... ስትራተጂስት፤ "...እኔ የሮማ ጠቅላይ ገዥ ሆኜ ስሔድ ያን ግዜ ጣሊያኖች ሰሐጢ ድረስ ሊመጡ ይችላሉ። አንዴ ክንዴን አሳይቻቸዋለሁ እንደገና ከመጡም እደግማቸዋለሁ! ራሱ ቀይ ባህር የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ወሰን ሆኖ ኖሯል፤ ይኖራልም..." በሚለው ዘመንን ተሻጋሪ አባባላቸው አለም የሚያውቃቸው ነበሩ።

"የምኒልክ ሰራዊት አንቀሳቃሽ ሞተር" በሆነው አሉላ ጉዳይ ላይ ገፋ አድርገው እንደሄዱት፣ እንደ ፕሮፌሰር ንጉሴ አየለ (ተደጋግሞ በሚገለፅላቸው "Ras Alula and Ethiopia`s Struggle Against Expansionism and Colonialism: 1872-1897" ስራቸው) ገለፃ ራስ አሉላ በስተኋላ ወደ ደጃዝማች በዝብዝ ካሳ (ኋላ አፄ ዮሐንስ 4ተኛ) ቤት ከተዛወሩ በኋላ ሹመትን በሹመት በመደረብ ወደ ፊት ገሰገሱ፡፡ በመጀመሪያ እልፍኝ አስከልካይ ቀጥሎም አጋፋሪነትን ተሾሙ፡፡ በ1873 ደጃዝማች ካሳ ንጉሰ ነገስት አጼ ዮሐንስ አራተኛ ሲባሉ አሉላ የሻለቅነትን ማዕረግ የንጉሱ ሊጋባነት ማዕረግን ደርበው ያዙ፡፡

ኢትዮጵያን ካቀኑት፤ እንደ አገርም ካቆሙት መካከል አንዱና ፊት መሪው አሉላ ሲሆኑ፤ ለዚህም፣ አሁን አሁን ነገር አለሙ ሁሉ ተደበላለቀ እንጂ፣ ኢትዮጵያ ስማቸውን ሳታነሳ ውላና አድራ አታውቅም ነበር። በተለይ በዘመነ ደርግ ታሪካቸው ልዩ የሚዲያ ሽፋን እንዲያገኙ ከሚደረግላቸው ባለ ታሪኮች መካከል አሉላ ቀዳሚው ነበሩ። በማስተማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ሁነኛ ቦታ ካላቸው ስመ ጥር ስብእናዎች መካከል አንዱ እኝሁ እያወራንላቸው ያሉት ብሄራዊ አርበኛና የጉራዕው አንበሳ፣ የጉንደቱ ሳቢሳ አሉላ አባ ነጋ ናቸው።

ሁለቱ አበይት ጦርነቶች (የ1875 የጉንደት እና የ1876 የጉራዕ) ሲሆኑ፤ በሁለቱም ጦርነቶች ወራሪዎቹ ግብፆች፣ አጋዥ ቅጥረኛ ወታደሮች እና አማካሪ ጄኔራሎች ሽንፈትን ተጎንጭተው ተመልሰዋል፡፡ ይህ ሁሉ የሆነው በቀይ ባህሩ አንበሳ ራስ አሉላ አባ ነጋ ነው። (አዳራሽ ውስጥ ብንሆን "አንድ ግዜ እናጨብጭብለት እስቲ" ሳንል የምንቀር አይመስለኝም።)

ስለ አሉላ ባለ ውለታነት በዚህ ጽሑፍ ዳግም እናስታውስ እንጂ ማንነታቸው ሲገለፅ፣ ገድላቸው ሲብራራ፣ ስራዎቻቸው ሲተነቱ ... ዛሬ አዲስ አይደለም። በስራዎቻቸው የታሪክን ከርስ በደንብ አድርገው ከሞሉት መካከል አንዱ እሳቸው ናቸው። በአለማችን በስማቸው ሳይቀር ተፅእኖ የፈጠሩ አርበኞች አሉ ከተባለ፤ ያለ ምንም ጥርጥር አሉላ ከፊት ይቆማሉ።

ለዚህ ደግሞ የታሪክ ተመራማሪው ፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስት ልጃቸውን አሉላ ማለታቸውን (ስለ አሉላ የሰሯቸውን ስራዎች ትተን) እንደ አንድና ተጨባጭ ማሳያ ነው።

በአንድ ወቅት፣ ዘሪሁን አበበ ይግዛው የተባሉ በ"አዲስ ጉዳይ" መጽሔት ላይ፣ የህዳሴ ግድባችንን የመሰረት ድንጋይ መጣል አስመልክተው "የ'ጉ' ቤት ለግብፆች" ሲሉ ባሰፈሩት፣ የመህዲስቶች ውጋት፣ የፋሺስቶች ጣሊያን መቅሰፍት የሆነው ጀግናው አሉላን አስታዋሽ መጣጥፍ ላይ እንዳሰፈሩት፤ አሉላ በ"ጉንደት—- ጉራዕ— " የፈፀሙት ጀብድ በ"ጉባ—-"ም ተደገመ የሚል የደስ ደስ ያለው ዜና መሳይ ጽሑፍ ሲሆን፤ ሀሳቡ ታሪካዊ መሰረት ያለው መሆኑንም ልብ ማለት ያስፈልጋል። (ሁለቱ "ጉ—"ዎች - የጉንደት፣ የጉራእ መሆናቸውን፤ የመጀመሪያው ከመጋቢት 7 ቀን እስከ መጋቢት 9 ቀን 1876 መካሄዱን ልብ ይሏል)፤ ሶስተኛው "ጉ—" የአባይ መገደቢያ ስፍራን የሚመለከተው "ጉባ"ን ባገናዘበ መልኩ ታሪክን በማገናኘት የቀረበ ጽሑፍ ነው። ለአጥኚና ተመራማሪ የተመቸ ደስ የሚል "ቀመር"። (በወቅቱ የጉራዕው ጦርነት - ግብፅ ኢትዮጵያን ለመያዝ የተነሳችበት አበይት ምክንያት አባይን ከነ ምንጩ የግብፅ ወንዝ ለማድረግ ከነበራት ቅዠት የመነጨ እንደ ነበር ልብ ይሏል፡፡)

በርእሳችን ስለ ራስ አሉላ እንግዳ ያልተነገሩ ጉዳዮችን ይዘን እንደ መጣን ተናግረናል። "ያልተነገሩ" የሚለው "በአግባቡ ከትውልድ ወደ ትውልድ ያልተላለፉ" ከሚለው ጋር በተለዋዋጭነት እንዲነበብ እያሳሰብን ወደ አልተነገሩቱ እንዝለቅ።

አሉላ ካልተነገሩለት ስራዎቹ መካከል የተሳተፈባቸው ዋና ዋና ጦርነች፤ ከእነ ማን ጋር እንደተፋለመና እነ ማንን ድል እንዳደረገ አለመታወቁ ነው። ከጦርነቶችና ድሎቻቸው እንጀምር።

በአገር አንድነት፣ ሉአላዊነት፣ ዳር ድንበር መከበር፣ በሕዝቦች አንድነትና በኢትዮጵያ ታሪክ የማይደራደሩት "የኢትዮጵያ ጦር ኃይል ጠቅላይ መሪ" (በ"መስከረም"፣ "በኢትዮጵያ ሕዝብ የነፃነት ትግል የአሉላ አባ ነጋ ሚና" ርእስ ስር እንደ ሰፈረው) ራስ አሉላ ከ24 በላይ በሆኑ ግዙፍ ጦርነቶች ላይ የተሳተፉ (በመምራት) ሲሆን፣ ከእነዚህም መካከል ከየካቲት 7 እስከ 9፣ 1876 (ከኦቶማን - ግብፅ ጋር) በጉራዕ፤ መጋቢት 8 እስከ 11፣ 1889 (ከመህዲስቶች ጋር) ጋላባት፤ ከጥር 7 እስከ 18 (ከጣሊያን ቅኝ ገዥዎች ጋር) መቀሌ፣ 1886፤ የካቲት 2፣ 1896 (ከጣሊያን ቅኝ ገዥዎች ጋር) አድዋ እና ሌሎች በርካቶች የሚጠቀሱ ሲሆን፤ "ሲጋልብ የመጣን አህያ ቀርቀብ አድርገህ ጫነው" እንዲል ስነቃላችን፤ ሁሉም በአሉላ ድል አድራጊነት የተጠናቀቁ ናቸው።

ሌላው ስለ አሉላ ለዚህ ትውልድ ያልተነገረው (ሊነገረው ሲገባ) መሰረታዊ ጉዳይ ዲፕሎማሲያዊ ተሳትፏቸውና ከውጪ መንግስታት ተወካዮች ጋር ያደረጓቸው ኦፊሴላዊ ስብሰባዎች (1879–1896) ሲሆኑ፤ ከሐምሌ አጋማሽ 1879 ጀምሮ እስከ ሀምሌ 1896 ድረስ ብቻ አገራቸውን በመወከል ከ24 በላይ ኦፊሴላዊ ስብሰባዎችን አድርገዋል።

ካደረጓቸው ኦፊሴላዊ ስብሰባዎች መካከል የግሪክ ቆንሲል፣ የብሪታኒያ መልእክተኛ፣ የፈረንሳይ መልእክተኛ፣ የኢጣሊያ መልእክተኛ፣ የሩሲያ መልእክተኛ፣ የብሪታኒያ ግብፃዊያን መልእክተኛ፣ የኢጣሊያ ወኪሎች፣ በኤርትራ የኢጣሊያ ገዥ፣ የብሪታኒያ ወኪል እና ሌሎች በርካቶች የሚገኙ ሲሆን፤ በአንዳቸውም ስብሰባና ውይይቶች የአገራቸውን ጥቅም አሳልፈው አልሰጠም።

ዶ/ር ንጉሴ አየለ የአድዋ 100ኛ አመትን አስመልክቶ በተዘጋጀው ልዩ እትም ("መስከረም" መጽሔት፤ በእውነቱ ለአሉላ እንደዛ አይነት ልዩ የመዘከር ስራ ተሰርቶ የሚያውቅ ስለ መሆኑ ይህ ጸሐፊ አያውቅም) ላይ እንዳሰፈሩት ይህ ሁሉ ቁርጥ የሆነ የአሉላ ኢትዮጵያዊ አቋም እስከ መጨረሻው የዘለቀ ሲሆን "ከአድዋ ድል በኋላ በ1897፣ የኢጣሊያኖች፣ እንግሊዞችና ፈረንሳዮች ከኢትዮጵያ ጋር ስለ ድንበር ለመደራደር፤ የኢትዮጵያን ነፃነትም ለመቀበል ተገደዋል።"

ሌላው ብዙዎቻችን በጉራእ እና ጉንደት ብቻ ስለምናውቃቸው፣ "የጦር ብልሀት ስለነበራቸውና እና የተዋጣለት ዲፕሎማትም ስለነበሩት"፣ ስለ አሉላ እንግዳ በሚገባ ያልተነገረውና ለትውልድ ያልተላለፈው በውጭው አለም የፈጠሩት ተፅእኖ ነው።

በዚሁ ከላይ በጠቀስነው መጽሔት ላይ በሚገባ ተብራርቶና በመዘርዝር (ቢቢሊዮግራፊ) መልክ እንደ ቀረበው፣ ከተነገረላቸው ይልቅ ያልተነገረላቸው የሚበዛው ራስ አሉላ፣ በመላው አለም ማለት ይቻላል፣ ርእስና ርእሰ ጉዳይ ሳይሆኑ ያለፉበት ጊዜ አለመኖሩ ነው። አዎ፣ በጀግንነታቸው ተወዳዳሪ የሌላቸው፣ በፅኑ ኢትዮጵዊነታቸው ውልፊትን የማያውቁት፣ በዲፕሎማቲክ ግንኙነታቸው የአገራቸውን ጥቅም በማስቀደም የሚታወቁት፤ በሳል የጦር መሪው፤ ስለ ራስ አሉላ እንግዳ ያልፃፈ የፕሬስ፣ ያላስተጋባ የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ አልነበረም (ዝርዝሩን ከመጽሔቱ ይመለከቷል)። እሳቸውን እያነሳ ያልተወያየ የአገራት መሪ፣ ስለ እሳቸው ያለውን እውቀት ያልወረወረ የታሪክ ፀሀፊም ይሁን የፖለቲካ ተንታኝ አልነበረም።

134ኛ ዓመት መታሠቢያቸውን ምክንያት በማድረግ በተዘጋጀው ፅሁፍ መግቢያ ላይ "ከዶጋሊው ድል በኋላ ጣሊያን ቀርቶ መላው አውሮፓ በፍርሃት ንዷል። ይህንንም ለማረጋጋት በኢጣሊያ ሮም ከተማ ውስጥ "Termini" ከሚባል ባቡር ጣቢያ ፊት ለፊት ባለ "piazza dei cinquecento' በሚባል ትልቅ አደባባይ ላይ በዶጋሊ ጦርነት ለሞቱ 500 የኢጣሊያ ወታደሮች ሰኔ 5 ቀን 1887 እ.ኤ.አ የመታሰቢያ ሐውልት ቆመላቸው፡፡ ራስ አሉላ ደግሞ በኢትዮጵያዊያን ልብ ውስጥ ሐውልታቸውን ሰርተው ጀግንነታቸው በውጪ አገር ዜጎች ሳይቀር አሁንም ድረስ እንደተተረከ ቀጠለ፡፡" በሚል የሰፈረውም እያልን ላለነው መረጃም ማስረጃችንም ነው።

ባጭሩ፣ አሉላ ድፍን የነጩን አለም ያንቀጠቀጡ፣ ቆፍጣናና የጀግኖች ቁና የነበሩ ሰው ናቸው። ይህ "በጉራዕ እና በጉንደት ..." ከሚሉት ግዙፍ (ግን ደግሞ ጥቂት) ድሎቻቸው በስተቀር፣ በሚገባ አልተነገረላቸውም። ስራቸው እንደ አንድ የኢትዮጵያ መስራች አባትነት ከትውልድ ወደ ትውልድ ይተላለፉ ዘንድ አላደረጋቸውም። ይህን ማድረግ ደግሞ የዚህ ትውልድ ስራ ነውና ሳይርቅ በቅርቡ .... ማለት ያስፈልጋል።

አሉላ በምኒልክ አድዋን ዋና ከተማቸው አድርገው የትግሬን ብዙውን የ7ሰሜን ክፍል እንዲገዙ ሾመዋቸዋል፤ የካቲት 15፣ 1897 ሕይወታቸው እስኪያልፍ ድረስም በዚሁ ስልጣናቸው ላይ ነበሩ።

# ስፖርት



## ለተሰንበት ግደይ ለመጀመሪያ የማራቶን ውድድሯ ቫሌንሲያ መርጣለች

**ቦጋለ አበበ**

የወቅቱ የረጅም ርቀት ድንቅ አትሌት ለተሰንበት ግደይ ስኬታማ ጊዜን እያሳለፈችበት ከሚገኘው የረጅም ርቀት ውድድሮች በቅርቡ ፊቷን አዙራ ወደ ማራቶን ለማተኮር እንዳሰበች ፍንጭ ሰጥታለች። ለዚህም በቀጣዩ ሐምሌ የመጀመሪያ የማራቶን ውድድሯን ለማድረግ የስፔኗን ከተማ ቫሌንሲያን ምርጫዋ እንዳደረገች ታውቋል።

አርባ ሁለተኛው የቫሌንሲያ ማራቶን ከወራት በኋላ ሲካሄድ የአለማችን የረጅም ርቀት ኮከብ የሆነችው ኢትዮጵያዊት አትሌት ለተሰንበት በአርባ ሁለት ኪሎ ሜትር የመጀመሪያ ውድድሯን በሩጫዋ ከተማ ቫሌንሲያ ለማድረግ የወሰነችው ካለምክኒያት አይደለም። ቫሌንሲያ የሩጫ ከተማ ብቻ ሳትሆን የተለያዩ የዓለም ክብረወሰኖች ከቅርብ አመታት ወዲህ የሚሰበርባት ሆናለች። በተለይም ይህች ከተማ ለለተሰንበት የተለየ ቦታ አላት። ለተሰንበት ባለፉት ጥቂት አመታት የዓለማችንን ታላላቅ አራት ክብረወሰኖች በማሻሻል አስደናቂ ብቃቷን ስታሳይ ሁለቱን ማሳካት የቻለችው በቫሌንሲያ ከተማ ነው።

የ2022 የዓለም ትልቁ አትሌቲክስ ቻምፒዮና በአሜሪካ ፖርትላንድ ኦሪገን ከጥቂት ወራት በኋላ እንደሚካሄድ ይታወቃል። የዓለማችን ድንቅ ድንቅ አትሌቶች ለራሳቸው ዝናና ስኬት እንዲሁም ለአገራቸው ክብር እልህ አስጨራሽ ተጋድሎ በሚያደርጉበት የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ለተሰንበትም በአስር ሺ ሜትር እንደምትወዳደር ይጠበቃል። ከዓለም ቻምፒዮናው ጥቂት ወራት በኋላ ግን በረጅም ርቀት ጣፋጭ ድሎችን በተቀዳጀችባት ቫሌንሲያ ከተማ በማራቶን ተጨማሪ ስኬት ለመጎናጸፍ እንደምትዘጋጅ የውድድሩ አዘጋጆች ማረጋገጣቸውን ሰሞኑን አሳውቀዋል።




የረጅም ርቀት የወቅቱ ኮከብ አትሌት ለተሰንበት ግደይ የመጀመሪያ የማራቶን ውድድሯን በቫሌንሲያ ለማድረግ ቀጠሮ ይዛለች፣

"የመጀመሪያ የማራቶን ውድድሬን በቫሌንሲያ እንደማደርግ ስገልጽ በደስታ ነው፣ ከቫሌንሲያ ጋር የተለየ ግንኙነት አለኝ፣ 2020 ላይ የ5ሺ ሜትር ክብረወሰንን፣ 2021 ላይ ደግሞ የግማሽ ማራቶን ክብረወሰንን በቫሌንሲያ በማሻሻል ልዩ ትዝታ አለኝ፣ በመጪው የቫሌንሲያ ማራቶንም ድንቅ ጊዜ እንደማሳልፍ ተስፋ አለኝ" በማለት ለተሰንበት መናገሯን አትሌቲክስ ዊክሊ ጽፏል።

የውድድሩ አዘጋጆች በበኩላቸው "የዓለማችን ድንቅ አትሌት ከሆኑት አንዷ ለተሰንበት ግደይ በቫሌንሲያ ማራቶን እንደምትሳተፍ ማረጋገጧ ከተማችንን የዓለማችን የሩጫ መዲና ለማድረግ እያሳየነው ያለውን ትጋት ያረጋግጣል፣ብዙ የዓለማችን ከተሞች እንደ ለተሰንበት ያሉ ድንቅ አትሌቶች የመጀመሪያ የማራቶን ውድድራቸውን እነሱ ጋር እንዲያደርጉ ፍላጎት አላቸው፣ ለተሰንበት እኛን ምርጫዋ በማድረጓ ኩራት ይሰማናል" በማለት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

ለተሰንበት ከቫሌንሲያ ጋር የተዋወቀችው 2020 ላይ አስደናቂውን የ5ሺ ሜትር የዓለም ክብረወሰን በማሻሻል ነበር። ይህች ኮከብ አትሌት ለአስራ ሁለት አመታት በሌላኛዋ ኢትዮጵያዊት የረጅም ርቀት ፈርጥ ጥሩነሽ ዲባባ ተይዞ የቆየውን የ5ሺ ሜትር ክብረወሰን 14:06:62 በመሮጥ አሻሽላ ዓለምን አስደምማለች። ከአመት በኋላ ወደ ቫሌንሲያ ተመልሳም 2021 ላይ የመጀመሪያ የግማሽ ማራቶን ውድድሯን በማድረግ 1:02:52 በሆነ ሰዓት የርቀቱን የዓለም ክብረወሰን ጨብጣለች።

ባለፉት ሁለት አመታት አስደናቂ ብቃቷን በተለያዩ የረጅም ርቀት ውድድሮች በማሳየት አራት ታላላቅ ክብረወሰኖችን በእጇ ያስገባችው ለተሰንበት በቫሌንሲያ ካሻሻለቻቸው ሁለት ክብረወሰኖች በተጨማሪ በኔዘርላድስም ትልቅ ስም ያስገኙላትን ሁለት ክብረወሰኖች መስበሯ ይታወቃል። ይህም በ2019 ኒጅመን አስራ አምስት ኪሎ ሜትር የጎዳና ላይ ውድድር የርቀቱን ክብረወሰን 44:20 በሆነ ሰዓት ያሻሻለችበት ነው። ለተሰንበት በ2020 ቶኪዮ ኦሊምፒክ የኢትዮጵያውያን ማጣሪያ ውድድር ሄንግሎ ላይ የሰበረችው የ10ሺ ሜትር ክብረወሰን ግን ከሁሉም የላቀ ነበር። የዚህን ርቀት ክብረወሰን ትውልደ ኢትዮጵያዊቷ የኔዘርላንድስ አትሌት ሲፈን ሃሰን በእጇ አስገብታ አርባ ስምንት ሰዓት ሳይሞላው ለተሰንበት በሄንግሎው የማጣሪያ ውድድር 29:01:03 በሆነ ሰዓት የግሏ ማድረግ የቻለችበት አጋጣሚ ያልተጠበቀና ብዙዎችን ያስደመመ ታሪክ ሆኖ ይታወሳል።

ለተሰንበት እነዚህን ታላላቅ ክብረወሰኖች እጇ ባስገባችበት የውድድር አመት በቶኪዮ 2020 ኦሊምፒክ በተለይም በ10 ሺ ሜትር ከፍተኛ የአሸናፊነት ግምት ተሰጥቷት የነበረ ቢሆንም አስራ ዘጠኝ ዙሮችን ለብቻዋ እየመራች የሚያግዛት ሌላ ኢትዮጵያዊ አትሌት ባለማግኘቷ የወርቅና የብር ሜዳሊያውን በትውልደ ኢትዮጵያውያኑ የኔዘርላንድስና የባህሬን አትሌቶች ሲፈን ሃሰንና ቃልኪዳን ገዛኸኝ ተነጥቃ የነሐስ ሜዳሊያ ማጥለቋ ይታወሳል።


## አገር አቀፍ ግልፅ የጨረታ ማስታወቂያ ቁጥር ብግጨ05/2014

የአማራ ክልል ፖሊስ ኮሌጅ ለሰልጣኞች አገልግሎት የሚውሉ የተለያዩ እቃዎችን ለማሟላት ቀጥሎ የተዘረዘሩትን በብሔራዊ ግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡

በመሆኑም፡-

1ኛ የምግብ ፍጆታዎች

2ኛ. የሰልጣኝ አልባሳት

3ኛ. የጽህፈት መሳሪያ

4ኛ. የጽዳት እቃዎች

**ስለሆነም ተወዳዳሪዎች፡-**

1. የዘመኑ ግብር የከፈሉበትን የታደሰ የንግድ ፈቃድ እና የግብር ከፋይነት ማስረጃ/TIN/ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
2. ከብር 200,000.00(ሁለት መቶ ሺህ ብር) በላይ ለሆነ ግዥ የቫት ተመዝጋቢ ማስረጃ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
3. በጨረታው ለመሳተፍ 1% የጨረታ ማስከበሪያ በጥሬ ገንዘብ ወይም በሲፒኦ /CPO/ ብቻ ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡
4. የጨረታውን ሰነድ ደብረ-ማርቆስ ከተማ በአዲሱ ግቢ አማራ ክልል ፖሊስ ኮሌጅ ድረስ በመምጣት የማይመለስ ብር 100.00(አንድ መቶ ብር) በመክፈል እስከ 15ኛው ቀን ድረስ መግዛት አለባቸው፡፡
5. ጨረታው በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በተከታታይ 15 ቀናት አየር ላይ ከዋለ በኋላ በ16ኛው ቀን ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ላይ ታሽጎ በዚሁ ቀን 3፡30 ሰዓት ይከፈታል፡፡ ሆኖም 16ኛው ቀን የስራ ቀን ካልሆነ ቀጥሎ ባለው የስራ ቀን ከጠዋቱ በ3፡00 ሰዓት ይከፈታል፡፡
6. ጨረታው በ16ኛው ቀን ተወዳዳሪዎች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በኮሌጁ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው ስፍራ ይከፈታል፡፡ ይሁን እንጂ የተወዳዳሪዎች አለመገኘት የጨረታውን መከፈት አያግድም፡፡
7. የእቃዎችን ዓይነት እና ዝርዝር መግለጫ ከጨረታ ሰነዱ ላይ ማግኘት ይቻላል፡፡
8. ኮሌጁ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡ **ለተጨማሪ ማብራሪያ ስልክ ቁጥር 0587714207/0587714199**

**የአማራ ክልል ፖሊስ ኮሌጅ**

## በድጋሚ የወጣ ግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ

በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በዋግኽምራ አስተዳደር ዞን የፃግብጂ ወረዳ ገ/ኢ/ል/ጽ/ቤት ለፃ/ወ/ሴ/መ/ቤቶች አገልግሎት የሚውሉ አላቂ እቃዎች የፅዳት እቃዎች ፈርኒቸር የመኪና ጎማ ደንብ ልብስ እቃዎችን እና የህትመት ውጤቶች አጫርቶ መግዛት ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቱን የምታሟሉ ተጫራቾች መወዳደር የምትችሉ መሆኑን ይጋብዛል።

1. በየዘርፉ የታደሰ ንግድ ፍቃድ ያላቸው

2 የዘመኑን ግብር የከፈሉ መሆናቸውን ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ

3. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር(TIN)

4. ተጫራቾች በጨረታው ለመሳተፍ ከላይ ከተራ ቁጥር 1-4 የተጠቀሱትንና የሚመለከታቸውን ማስረጃዎች ፎቶ ኮፒ ከመጫረቻ ሰነዶቻቸው ጋር አያይዘው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

5. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ቢድ ቦንድ/1%/ በጥሬገንዘብ ወይም ሲፒኦ ማስያዝ አለባቸው

6. የእቃዎቹን አይነት ዝርዝር መግለጫ /ስፔስፊኬሽን ከጨረታ ሰነድ ማግኘት ይችላሉ

7. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን የማይመለስ ብር 50 /ሃምሳ ብር ብቻ/ ፅ/ቤቱ በጊዜያዊ ከተቀመጠበት ዋ/ዞ/ገ/ኢ/ል/ መምሪያ ሰነዱን በመግዛት ጨረታው በግልጽ ጨረታ ከወጣበት ከ 12/9/2014 ዓ/ም እስከ 26/9/2014 ዓ/ም ጀምሮ ለተከታታይ 15 ቀናት በጊዜያዊው ቢሮ ዋ/ዞ/ገ/ኢ/ል/ መምሪያ በመምጣት መውሰድ ይችላሉ፡፡

8 ማንኛውም ተጫራች የጨረታ ሀሳቡን በአንድ ወይም አንድ ወጥ በሆኑ ሁለት ቅጆች ማለትም ዋናና ቅጅ በማለት በጥንቃቄ በታሸገ ፖስታ በጊዜያዊው ቢሮ ዋ/ዞ/ገ/ኢ/ል/መምሪያ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ዘወትር በስራ ሰዓት ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡

9. ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በ27/9/2014 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡30 ሰዓት ላይ ታሽጎ በዚሁ ቀን 4፡30 የሚከፈት መሆኑን እንገልጻለን፡፡

10.መ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው

11, ጨረታው ስርዝ ድልዝ ወይም የማይነበብ ሰነድ ተቀባይነት የለውም።

12. በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ ሁሉ የጨረታው ዝርዝር መረጃ ከፈለጉ በወረዳው ጽ/ቤቱ ድረስ በአካል በመገኘት ወይም መረጃ ማግኘት ይችላሉ፡፡

**በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በዋግ ኽምራ ዞን የፃግብጂ ወረዳ ገ/ኢ/ል/ጽ/ቤት /ፃታ/**